# ኢፕድ አዲስ ዘመን

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 314 ሐምሌ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## የገንዘብ ፖሊሲው ዘመናዊ የባንክ አሠራርን ያመጣ ይሆን?

ዘሳለም ግዛው

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንኩን የፖሊሲ ተመን መወሰን፣ የሰነዶች ግብይት ጨረታ መጀመር፣ የአንድ ቀን የብድር እና የገንዘብ አገልግሎት ማስተዋወቅና የባንክ ለባንክ የገበያ ሥርዓት ማስተዋወቅን ያካተተ አዲስ የፖሊሲ ማዕቀፍ በቅርቡ ይፋ አድርጓል።

አዲሱ ፖሊሲ የባንኩን አሠራር የሚያዘምን፣ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር የተጣጣመ፣ ለፈጣን፣ ፍትሃዊ እና ሥራ ፈጣሪ የኢኮኖሚ ልማት የሚረዳም መሆኑን የባንኩ ገዢ ማሞ ምህረቱ ተናግረዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ክቡር ገና ባንኩ ይፋ ያደረገው አዲሱ ፖሊሲ ወደ ዘመናዊ የባንክ አሠራር የሚያሸጋግር፣ ባንኮች የተረጋጋ አሠራር እንዲኖራቸው የሚያስችል መሆኑን ያመለክታሉ።

የገንዘብ ፖሊሲው ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል











## ‹‹ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጥ የሰው ኃይል የማፍራት ሥራው ውጤት እያሳየ ነው››

ወይዘሮ ሎሚ በዶ
- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ

ዘሳለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- በትጋት ሠርተው ድህነትን የሚያሸንፉ፣ ለማክሮ ኢኮኖሚው እድገት የራሳቸውን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱና ሁለንተናዊ ብልጽግናን የሚያረጋግጡ የሠለጠነ የሰው ኃይል የማፍራት ሥራው ስኬት እየታየበት እንደሚገኝ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባዔ ሎሚ በዶ ገለጹ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ጋር በፖሊሲና በሥራ ፈጠራዎች ዙሪያ ትናንት ውይይት አካሂዷል።

የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ዜጎች እንደፀጋዎቻቸው እንዲሠሩ፤ ተኪ ምርቶችን እንዲያመርቱና ህብረተሰቡን ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ታስቦ እየተተገበረ የሚገኘው ሥራ አበረታች መሆኑን ምክትል አፈ ጉባዔ ሎሚ በዶ ተናግረዋል።

በሰላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት፣ የሙያ ደህንነትና ጤንነት፣

‹‹ሁለንተናዊ ብልጽግናን...ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## በተሰበሰበው ገቢ በመዲናዋ ከ18 ሺህ በላይ የልማት ፕሮጀክቶች ተሠርተዋል

ሔርሞን ፍቃዱ



አዲስ አበባ፡- ባለፈው በጀት ዓመት ከግብር ከፋዮች በተሰበሰበው ገቢ የከተማዋን ነዋሪዎች የኑሮ ጫና የሚያቃልሉ እና የከተማዋን ገጽታ የቀየሩ 18 ሺህ 091 የልማት ፕሮጀክቶችን መሠራታቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናገሩ።

የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ ትናንት በአዘጋጀው የገቢ ንቅናቄ መድረክ የተገኙት ከንቲባዋ

በተሰበሰበው ገቢ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የሁለተኛ ትልውድ አረንጓዴ ዐሻራ

ጌትነት ተስፋማርያም

ዜና ሐተታ

የምትተክል ሀገር፣ የሚያፀና ትውልድ" በሚል መሪ ሃሳብ በተጀመረው የዘንድሮውን የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ላይ መላው ኢትዮጵያውያን እየተሳተፉ ነው። ከኢትዮጵያውያን ባሻገር ለእንግድነት ወደ መዲናዋ ጎራ ያሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ጭምር ችግኝ በመትከል በአካባቢ ጥበቃ ላይ እንዲሳተፉ እየተደረገ ነው።

ከተለያዩ አህጉራት የመጡ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያንም የዚህ የአካባቢ ጥበቃ አካል ለመሆን

የሁለተኛ ትልውድ...ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# በዞኑ በሮዝመሪ ምርት ከ19 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ እየሆኑ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በአሁኑ ጊዜ ሮዝመሪ በማልማት ከ19 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን የስልጤ ዞን ግብርና መምሪያ አስታወቀ።

የዞኑ ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ሙርሰል አማን ለኢትጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በምርት ዘመኑ የሮዝመሪ ምርት ሽፋንን አራት ሺህ 678 ሄክታር በማድረስ ከ70 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለገበያ ቀርቧል። በዚህም ከ19 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ ሆነዋል።

ሮዝመሪ በማልማት በአሁኑ ጊዜ ከ19 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ሙርሰል፤ በዘንድሮ የምርት ዘመንም አንድ ሺህ 779 ሄክታር በአዲስ መሬት በማልማት አጠቃላይ በሮዝመሪ የተሸፈነውን መሬት ስድስት ሺህ 457 ሄክታር ለማድረስ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በስልጤ ዞን የሮዝመሪ ልማት በሶስት ወረዳዎች ይለማ ከነበረበት ባለፈው ዓመት ወደ 10 ወረዳና ሶስት ከተማ አስተዳደሮች እየለማና እየተስፋፋ መሆኑን የሚናገሩት የግብርና መምሪያ ኃላፊው፤ የሮዝመሪ ቅመምን በስፋት በማምረትም የምርት አቅርቦትና ለውጭ ገበያ በማቅረብ የሚገኘው ገቢ እያደገና የአርሶ አደሩም ተጠቃሚ እየሆነ መምጣቱን ጠቁመዋል።

ዘንድሮም የሮዝመሪ ምርት ሽፋንን አራት ሺህ 678 ሄክታር መሬት በማድረስ ከ70 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ለገበያ ቀርቧል። ከዚህ ውስጥ 25 ሺህ 750 ኩንታሉን ወደ ውጪ በመላክ አራት ነጥብ ስድስት



ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን አመልክተዋል።

በዞኑ 2014/15 ምርት ዘመን 49 ሺህ 550 ኩንታል የሮዝመሪ ምርት ተመርቶ ለማዕከላዊ ገበያ መቅረቡን ያነሱት አቶ ሙርሰል ፤ ለማዕከላዊ ገበያ ከተላከው ምርት ውስጥም 13 ሺህ 799 ኩንታሉን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ዶላር ተገኝቶ እንደነበር አስታውሰዋል።

እንደ መምሪያ ኃላፊው ገለጻ፤ በገቢ ደረጃ ከአምናው ጋር ሲነጻጸር እጥፍ ብልጫ ያለው ሲሆን ከሮዝመሪ በተጨማሪ በሌሎች አዋጭ በሆኑ መድሃኒታማና መዓዛማ ቅመሞች በተለይ ላቫንደር ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ሮዝመሪ በተለምዶ "የስጋ መጥበሻ" በመባል የሚታወቅ ሲሆን ለምግብ ማጣፈጫ፣ ለዘይት ምርት፣ ለመድሃኒት መቀመሚያና ለመዋቢያ አገልግሎቶች የሚውል በመሆኑ በዓለም ገበያ ተፈላጊነቱ እያደገ መጥቷል።

በኢትዮጵያ በአነስተኛ ጓሮ እንጂ በማሳ ላይ በስፋት ያልተለመደው ሮዝመሪ፤ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ ዞን በስፋት እየተመረተ ነው።

በዚህም ምርቱ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ወደ ውጭ ገበያ በማቅረብ የውጭ ምንዛሬ እያስገኘ እንደሚገኝ ይታወቃል።

# የልማት ድርጅቶች በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በአረንጓዴ ዐሻራም ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነው

## - የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር እና የብርሃንና ሰላም ድርጅት ሠራተኞች ችግኝ ተከሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ሞጆ፡- የልማት ድርጅቶች ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እያደረጉ እንዳሉት ሁሉ በአረንጓዴ ዐሻራም ውጤታማ ተግባር በማከናወን ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ገለጸ። የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር እና የብርሃንና ሰላም ድርጅት ሠራተኞች ችግኝ ተክለዋል።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር በሞጆ ሃዋሳ ፍጥነት መንገድ ከኢትዮጵያ ክፍያ መንገዶች ኢንተርፕራይዝና ጋር በመሆን የችግኝ ተከላ መርሃግብር ትናንት አካሂዷል።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ኃይለሚካኤል በወቅቱ እንደገለጹት፤ የልማት ድርጅቶች ዓለምአቀፍ ውጤታማና ተወዳዳሪ ሆነው የሀገርን ኢኮኖሚ ለማገዝ የሚያስችሉ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

የልማት ድርጅቶች አስተዋጽኦ ለሀገር አኮኖሚ ዕድገት ከሚያደርጉት አስተዋጽኦ በተጨማሪ በ2016 በጀት ዓመት ለ63 ሺህ 311 ዜጎች የሥራ ዕድል ፈጥረዋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም የልማት ድርጅቶች ምን ያህል ለማህበረሰባችን ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ እንዳሉ ማወቅ ይቻላል ብለዋል።

ሌላኛው ማሳያ ደግሞ አረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ከተጀመረ ጀምሮ ሀገራዊ ዓላማን ለማሳካት እያከናወኑት ያለው የችግኝ ተከላ መርሃግብር መሆኑን አውስተው፣ ይህም የልማት ድርጅቶች ለሀገር ግንባታ ያላቸውን ዘርፈ ብዙ ሚና የሚገልጽ ነው ብለዋል።

አቶ ሀብታሙ፤ የልማት ድርጅቶች ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ሁሉ በአረንጓዴ ዐሻራም ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ገልጸዋል።

በየዓመቱ አንድ ቀን ብቻ ችግኝ ተክለን መሄድ ሳይሆን የተከልናቸውን ችግኞችም በጀት መድበን



እየተንከባከብን የታለመላቸውን ዓላማ እንዲያሳኩ ጥረት ስናደርግ ቆይተናል ሲሉም ተናግረዋል።

በተመሳሳይ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ሠራተኞችና ከፍተኛ አመራሮች በትናትናው ዕለት በድሬ ግድብ አካባቢ ችግኝ ተክለዋል።

በወቅቱም ዋና ሥራ አስኪያጁ አቶ ሽታሁን ዋለ ፤ ተቋሙ የህትመት ግብዓት የሚያገኘው ከተፈጥሮች እፅዋቶች በመሆኑ በአረጓዴ ዐሻራ ከዛሬ 21 በፊት ጀምሮ በትኩረት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የድሬ ግድብ ሲሠራ አካባቢው የተራቆተ ነበር፤ የተራቆተውን መሬት በደን ሸፍኖ ግድቡ በደለል እንዳይሞላ ለማድረግ ለተከታታይ 21 ዓመታት ድርጅቱ ችግኝ የመትከል ፤ የተተከሉትን እንዲጸድቁ ሠራተኛ የመቅጠርና በእንሳሳት እንዳይጎዱ የማጠር ሥራ ሠርቷል ብለዋል።

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት በድሬ ግድብ አካባቢ ለ21 ዓመታት ያከናውነው አረጓዴ ዐሻራ ሥራ የማህበረሰቡን ምርትና ምርታማነት እያሳደገ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ድርጅቱ የድሬ ግድብ ሲገደብ ጀምሮ አካባቢውን በደን ለመሸፈን የተቀበለውን ሰፊ መሬት ሙሉ ለሙሉ ሸፍኖ ለሸገር ከተማ አስተዳደር አስረክቧል ብለዋል።

ችግኙን የተከሉት የተቋማቱ ሠራተኞች በበኩላቸው፤ የተከልናቸውን ችግኞች ከሚንከባከቡ ባለሙያዎች በተጨማሪ በየሶስት ወሩ የተከሉትን ችግኝ እንደሚንከባከቡ ተናግረዋል። ከዚህም ባለፈ ቀጣዩ ትውልድ አረንጓዴ ዐሻራን ሊያስቀጥል እንደሚገባ ገልፀዋል።

# በጎንደር ከተማ አንድ ነጥብ 66 ሚሊዮን ችግኞች ተተከሉ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር እስካሁን አንድ ነጥብ 66 ሚሊዮን ችግኞች መተከላቸውን የጎንደር ከተማ ግብርና መምሪያ አስታወቀ። በችግኝ ተከላ መርሐ ግብሩ 32 ሺህ 532 የህብረተሰብ ክፍሎች መሳተፋቸው ተመላክቷል።

በጎንደር ከተማ ግብርና መምሪያ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት ቡድን መሪ አቶ አስቻለው ወርቁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016/17 የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አራት ነጥብ 75 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ እስካሁን በተሠራው ሥራ አንድ ነጥብ 66 ሚሊዮን ችግኞች ተተክለዋል።

በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎችና በ11ዱ የገጠር ቀበሌዎች 475 ሄክታር መሬትን በችግኝ ለመሸፈን ታቅዶ፤ እስካሁን በተተከሉት ችግኞች 116 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት መሸፈን መቻሉን ገልጸዋል።

የችግኝ ተከላ መርሐ ግብሩ ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም መጀመሩን ገልጸው፤ በተከላ መርሐ ግብሩም 32 ሺህ 532 የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፈዋል ብለዋል።

የችግኝ ተከላውን ለማከናወን ችግኝ የማፍላት፣ ቦታ የመለየት እና በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተሠርተዋል ያሉት አቶ አስቻለው፤ በ2016 በጀት ዓመት ሶስት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ችግኞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ ሶስት ነጥብ 25 ሚሊዮን ችግኞችን ለተከላ ማዘጋጀት መቻሉን አስታውቀዋል።

ችግኞቹ የተዘጋጁት በከተማዋ በሚገኙ 463 የችግኝ ጣቢያዎች ሲሆን፤ ለተከላ የተዘጋጁት ችግኞች ሁለገብ መኖ፣ ፍራፍሬ፣ ቡናና ሌሎች ሀገር በቀል ዛፎች ናቸው ብለዋል።

ፌዴራል እና ክልል በሚያወጣው የአንድ ጀንበር የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር በሁሉም ቀበሌዎች በ11 የተከላ ሳይቶች 23 ነጥብ 57 ሄክታር መሬት መለየቱን ገልጸው፤ በእነዚህ ቦታዎች 195 ሺህ 500 ችግኝ ለመትከል እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በጊዜዊናትና በቋሚነት ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፈጠሩን ገልጸው፤ በዚህ ዓመት ብቻ ለ295 ሰዎች ቋሚ የስራ እድል ተፈጥሮላቸዋል ሲሉ አስረድተዋል።

ችግኝ መትከል ብቻ ግብ ባለመሆኑ ችግኞች ባለቤት ኑሯቸው ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው በትኩረት እየተሠራ ሲሆን፤ ጽድቀት መጠናቸውም ከዓመት ወደ ዓመት እየተሻሻለ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የአካባቢው ማህበረሰብ ችግኝ መትከል የሚያስገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በመረዳት ለ2016/17 የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ፣ ለችግኞች ጥበቃና እንክብካቤ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

በጎንደር ከተማ በአንገረብ የችግኝ ጣቢያ የሥራ እድል የተፈጠረላቸው አቶ ቸኮል እንየው በበኩላቸው፤ አርሶ አደሮች እና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች አትክልትና ፍራፍሬ፣ ሀገር በቀል እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው ችግኞችን በስፋት እንዲያገኙ መደረጉን አስታውቀዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሆርቲካልቸር ዘርፉን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ በመምራት የኢኮኖሚው አቅም ማድረግ ይገባል!

ኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ሀብቶች ባለቤት ናት። በተለይ የግብርናው ዘርፍ ዛሬም በኢኮኖሚው ቀዳሚ ባለድርሻ እንደመሆኑ፤ ይሄንን ዘርፍ በተገቢው መልኩ ተገንዝቦና አልምቶ የሀገርን ኢኮኖሚ ማላቅ እና የኢንዱስትሪውንም ሽግግር እውን ማድረግ የተገባ ነው።

ከዚህ አኳያ በሰብል ልማት የታየው ከፍ ያለ ውጤት፣ ግብርናው ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ ከተሠራበት እውነትም ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ መበልጸግ የምትችልበት አቅም እንዳላት ያመላከተ ነው። በተለይ በስንዴ ልማት ዘርፉ የተከናወነው ተግባር ኢትዮጵያን ከስንዴ ለማኝነት ወደ ስንዴ ላኪነት ያሸጋገራት ተግባር ነው።

በተመሳሳይ በሩዝ፣ በሻይ ቅጠል፣ በአቮካዶ፣ በቡና... በጥቅሉ በሰብል፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ዘርፉ እየተመዘገበ ያለው ውጤት፤ እንደ ሀገር በግብርናው ዘርፍ የልማት አቅሞችን ለይቶ መሥራት ከተቻለ እንደ ሀገር የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ከፍ ያለ የውጭ ምንዛሬ የገቢ ምንጭ መፍጠር እንደሚቻል በተግባር የገለጡ ናቸው።

ከእነዚህ አንዱ ደግሞ የሆልቲካልቸር ዘርፉ፣ በተለይም የአበባ ልማት ተጠቃሽ ነው። እንደሚታወቀው የአበባ ምርት በዓለም ገበያ ትልቅ ተፈላጊ እና ከፍ ያለ ገቢም የሚያስገኝ ነው። በዚህ በኩል በርካታ ሀገራት በአበባ ገበያው ላይ ጉልህ ስፍራን ይዘው፤ የሀገራዊ ገቢያቸውን ሲደጉሙ ይታያል።

ኢትዮጵያም በዚህ ዘርፍ ሩቅ የሚባል ታሪክ ባይኖራትም ላለፉት ሁለትና ሦስት አስርት ዓመታት በአበባ እርሻ ዘር ትልልቅ ሥራዎችን እየሠራች ትገኛለች። ለዚህም የአበባ እርሻ ስፍራዎችን በመለየት እና ባለሀብቶችን (አልሚዎችን) በመጋበዝ በሚፈለገው ልክም ባይሆን አበረታች ውጤት ማየት ተችሏል።

በዚህም በየዓመቱ በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ከአበባ ምርት ሽያጭ እየተገኘ የዘለቀ ሲሆን፤ እንደ ሀገር ከሚታዩ የሰላም ብሎም ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ጋር ተያይዞም ዘርፉ በበርካታ ውጣ ውረዶች ታጅቦ መዝለቁ፣ የገቢ መጠኑም በዚያው ልክ መውጣት መውረዱ አልቀረም። ከሰሞኑ የወጣ መረጃ እንደሚያመለክተውም እንደ ሀገር ከሆልቲካልቸር ዘርፉ በ2015 ዓ.ም 658 ሚሊዮን ዶላር፣ በ2016 በጀት ዓመት ደግሞ 535 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል። ከዚህ ውስጥ የአበባ ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል።

ዘርፉ በዚህ መልኩ ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍ ያለ ፋይዳ ያለው መሆኑ እሙን ቢሆንም፤ የአበባ እርሻ በአግባቡ እና በጥንቃቄ ካልተከናወነ ግን ከፍ ያለ አካባቢያዊም ሆነ የጤና ጉዳቶች እንዳሉት የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ። ጥናቶችም ይሄንኑ ያሳያሉ። ከዚህ አኳያ በኢትዮጵያም በተለይ ሥራው በአብዛኛው በሐይቆች አካባቢ የሚከናወን እንደመሆኑ፤ በሐይቆች ሥነሕይወታዊ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማድረሱ አልቀረም።

ለዚህ አንድ አብነት መጥቀስ ቢቻል፣ የባቱ (ዝዋይ) ሐይቅ አንዱ ሲሆን፤ በአካባቢው ያለ የአበባ እርሻም ሆነ ሌሎች ተያያዥ የግብርና ግብዓቶች ጋር ተያይዞ ወደ ሐይቁ አካል የሚገቡ ኬሚካሎች፣ በሐይቁ ውስጥ የሚገኙ የዓሳ ዝርያዎች ላይ ስጋት መደቀናቸው በተለያየ ጊዜ ሲገለጽ ቆይቷል።

ይሄ የሚያሳየው ደግሞ የአበባ እርሻ ለሀገር ኢኮኖሚ ከፍ ያለ ፋይዳ ያለውን ያህል፤ በአግባቡ ካልተመራ እና በጥንቃቄ ካልተሠራበት አካባቢያዊ ጉዳቱም የማይናቅ መሆኑን ነው። ከዚህ አኳያ በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ባለድርሻዎች ሃሳብና ሙያዊ አስተያየት ሲሰጡ ቆይተዋል። በመንግሥት በኩልም፣ በተለይ ዘርፉን በሚመራው አካል በኩል ጉዳዩን በማጤን፤ የሆልቲካልቸር ዘርፉ ጉዳት በመቀነስ እና ከፍ ካለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ለመቋደስ የሚያስችል ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።

ለዚህ ደግሞ ተጠያቂነትን በሚያስከትል መልኩ ዘርፉን አንድም በሕግ፣ ሁለትም በጠንካራ የተናበበ አሠራር መምራት የተገባ በመሆኑ፤ ብሔራዊ የሆርቲካልቸር ረቂቅ ስትራቴጂ ሰነድ፤ እንዲሁም በዘርፉ ያሉ አንኳር ችግሮችንና የመፍትሔ ሃሳቦችን ያጠቃለለ ብሔራዊ የ10 ዓመት ረቂቅ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ ውይይት ተደርጎበታል።

በዚህ ስትራቴጂ መሠረት የሆርቲካልቸር ዘርፉን ዓመታዊ ገቢ ማሳደግ ቁልፍ ተግባር ሲሆን፤ በዚህም በ10 ዓመታት ውስጥ ሦስት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ገቢ የማግኘት ግብ ተቀምጧል። ከዚህ በተጓዳኝም የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ፣ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን ለማሟላት፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን ማሳደግና የከባቢ ተጽዕኖውን መቀነስ የትኩረት አቅጣጫው ነው።

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ በአበባ፣ በአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም በሥራ ስር ልማት እምቅ አቅም አለ። የሆርቲካልቸር ዘርፉም የውጭ ምንዛሪ በማስገኘትና የሥራ ዕድል በመፍጠር በኩል ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ነው። ይሁን እንጂ ዘርፉ በብዙ ችግሮች ውስጥ እየዳከረ እንደመሆኑ፣ የሆርቲካልቸር ብሔራዊ ስትራቴጂ መዘጋጀቱ በዘርፉ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን በመፍታት፣ ዘርፉ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ የሚያስችል ነው። በመሆኑም የሆልቲካልቸር ዘርፉን ጥንቃቄ በተሞላበት መንገድ በመምራት ዘርፉን የኢኮኖሚው አቅም ማድረግ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ያልበረደው እሳት!

ዳንኤል ዘነበ

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 61/177 እ.ኤ.አ ታኅሣሥ 20 ቀን 2006 በመወያየት አንድ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን አጽድቋል። ዓለም አቀፍ ስምምነቱ የሰው ልጅ በአስገዳጅ ሁኔታ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣ ሕግ 'Disappearance Convention' በመባል ይታወቃል። በኮንቬንሽኑ ላይ ሰውን በአስገዳጅ ሁኔታ መሰወር፣ ከሕጋዊ ጥበቃ ውጪ መደበቅ፣ ሰዎችን ከሕግ ጥበቃ ውጪ እንዲሆኑ ማድረግ፣ አስገድዶ መሰወር እንደሆነ ተቀምጧል። እነዚህ ወንጀሎች በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሆነ በሀገር የውስጥ ሕጎች ላይ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑ ናቸው።

በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ፍጡርን የማገት ድርጊት ለየትኛውም ዓላማ ተፈጽሞ ቢገኝ በምንም ዓይነት አመክንዮ ሊደገፍ ወይም ቅጣቱ ሊለዝብ የማይችል ደረቅ ወንጀል እንደሆነ ተደንግጓል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 90 (1) ሥር በሰብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ብሎ ከዘረዘራቸው መካከል በአስገዳጅ ሁኔታ ሰውን መሰወር ይገኝበታል። የወንጀሉ ደረጃ ከባድ እና ከነጭራሹ አንዳች መንግሥታዊ ምህረትን ወይም ይቅርታን የማያሰጥ እንደሆነም ሕገ መንግሥቱ ላይ በማያሻማ ቋንቋ ተቀምጧል። ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ሰዎችን አስገድዶ የመሰወር (Enforced Disappearance) ወንጀል እየጨመረ መጥቷል።

ሰዎች በታጣቂዎች የመታገት ዜና እንግዳ መሆኑ ከቀረ ሰነባብቷል። ክስተቱም በተወሰኑ መጥፎ ዕጣ በገጠማቸው ሰዎች ላይ የሚከሰት ሳይሆን፣ በተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ እና በብዛት የሚያጋጥም ስጋት ሆኗል። በሁሉም አቅጣጫዎች፣ በሁሉም አጋጣሚዎችም ሆነ በሁሉም መስኮች እገታ ተፈጸመ ሲባል መስማት የተለመደ ወደ መሆን ተሻግሯል። የጭነትም ሆነ የሰው መጓጓዣዎች ተሽከርካሪዎች የእገታ ሰለባ ስለመሆናቸው በሰፊው ይሰማል። ከኢንዱስትሪዎች እስከ ቤተ እምነቶች የዕገታ ወንጀል ተቃጣባቸው መባሉ ተለምዷል።

መንግሥት ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ሰዎችን በማገት ገንዘብ መጠየቅ እየተለመደ መምጣቱን አምኗል። ወንጀሎቹ ለገንዘብ ወይም ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚውሉ መሆናቸውን እንዲሁም የፀጥታ መዋቅሩን በገንዘብ በመደለል የራሳቸውን የፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚያደርጉ ግለሰቦች እንደሚሳተፉ ጭምር ተናግሯል። በሀገሪቷ ዘላቂ ሰላም ለማስፈን መንግሥት በሁሉም አቅጣጫ ያለ ዕረፍት እየሠራ ቢሆንም፤ በታጠቁ ኃይሎች የሚፈጸመው ዕገታ እንደቀጠለ ነው።

> ዘላቂ ሰላም ለማስፈን መንግሥት በሁሉም አቅጣጫ ያለ ዕረፍት እየሠራ ቢሆንም፤ በታጠቁ ኃይሎች የሚፈጸመው ዕገታ እንደቀጠለ ነው

ሰሞኑን ከደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ወደቤታቸው በመመለስ ላይ የነበሩ ተማሪዎች ላይ የተፈጸመው ዕገታ በብዙዎች ዘንድ መረር ያለ ስሜት ፈጥሯል። ከእንዲህ ዓይነቱ ሰብዓዊነት የጎደለው ድርጊት የሚጠቀመው ማን ነው የሚለው ምላሽ የሚሻ ጥያቄ አስነስቷል። የወንጀል ድርጊቱ በተለይ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች መደጋገም ዜጎች ደህንነት እንዳይሰማቸው፤ በነጻነት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን ለማከናወን እንዲቸገሩ እና ኑሯቸው በስጋት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል።

በሀገራችን የድርጊቱ መደጋገም እየፈጠረ ካለው ውስጣዊ ችግርና ተፅዕኖ ባሻገር ውጫዊው ተጽዕኖው ከፍተኛ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ኢንቨስተርም ሆነ ቱሪስት ወደ ኢትዮጵያ ጉዞ ሲያቅዱ የመጀመሪያ ጥያቄያቸው ሰላም እንደሆነ ይታወቃል። ቱሪዝምና ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጋቸው ትልቁ ነገር ሰላማዊና የተረጋጋ ከባቢ ነው። ፖለቲካዊ ሆነ ገንዘብ በመፈለግ በየአካባቢው የሚፈጸሙ የእገታ ወንጀሎች ዕገታዎችና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ለቱሪዝምና ለኢንቨስትመንት ፀር ናቸው። ሰዎችን አስገድዶ የመሰወር (Enforced Disappearance) ወንጀል መጨመር ውስጣዊም ውጫዊም ተፅዕኖ ያለው አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን ተረድቶ መሥራትን ይጠይቃል።

መንግሥት ሰላምና ፀጥታን ለማስፈን የሚያደርገው ጥረት ላይ ጥላሸት እየቀባም ጭምር ነው። የፌዴራል ፖሊስ ሆነ መከላከያ የኅብረተሰብ ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር ኃላፊነቱን ለመወጣት ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም የጸጥታ አካላት ወንጀሎቹን ለመከላከል በቅንጅት ውጤታማ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ በተጨባጭ አሳይተዋል። ለምሳሌ በደባርቅ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተፈጸመው ዕገታ ተከትሎ አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል።

ለአብነት ይህን ጠቀስን እንጂ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ባደረገው ተጋድሎ በተለያዩ አካባቢዎች በታጠቁ ቡድኖች የታገቱ ዜጎችን በማስለቀቅ ሕዝባዊነቱን አስመስክሯል። በመጠኑም ቢሆን በድርጊቱ የተሳተፉ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን ተከታትሎ በመያዝ ተጠያቂ ሲሆኑ አይተናል። ነገር ግን የዕገታ ወንጀሉ እየተስፋፋበት ባለበት ልክ የመከላከልና መቆጣጠር ሥራው እየሄደ ነው ለማለት ያዳግታል። የዕገታ ድርጊቱ በተደጋጋሚ የሚፈጸምባቸው አካባቢዎች ላይ ዘላቂ መፍትሔ ባለመሰጠቱ በአካባቢዎቹ የሚኖሩ ሰዎች የእገታ ሰለባ እስከመሆን መድረሱ በምክንያትነት ይነሳል። በመንግሥት የፀጥታ መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦችን በመጠቀም የሚፈፀም ስለመሆኑም መንግሥት በተደጋጋሚ በተደረገ ምርመራ አረጋግጫለሁ ብሏል። መንግሥት የፀጥታ መዋቅር ውስጥ ያለውን ክፍተት በአግባቡ ባለመፈተሹ ችግሩ እንዲባባስ እንዳደረገው ይታመናል።

ስለሆነም መንግሥት በሀገራችን አሳሳቢ እየሆነ ለመጣው ሰዎችን አስገድዶ የመሰወር (Enforced Disappearance) ወንጀል አፋጣኝ መፍትሔ በመስጠት መንግሥታዊ ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል። ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ባሳተፈ መልኩ የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። በመንግሥት ፀጥታ መዋቅር ውስጥ ሆነው በድርጊቱ የሚሳተፉ ግለሰቦችን በአፋጣኝ ተጠያቂ ማድረግም ይጠበቅበታል። እንዲህ ያሉ ግለሰቦች እሽሩሩ ሊባሉ የሚገባቸውም አለመሆናቸው መታወቅ አለበት።

በሕገ መንግሥቱ ላይ እንደተቀመጠው የወንጀሉ ደረጃ ከባድና ከነጭራሹ አንዳች መንግሥታዊ ምህረትን ወይም ይቅርታን የማያሰጥ መሆኑ ነው። በዚህ የወንጀል ድርጊቱ ተሳትፎ የሚያደርግን ማንኛውንም አካል መንግሥት ለሕግ ማቅረብ ግዴታ አለበት። የፌዴራል መንግሥት ሆነ የክልል የጸጥታ አካላት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚፈጸሙ እገታዎችን ለመከላከል የጀመሩትን ጥረት አጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

ኅብረተሰቡም መንግሥት ወንጀሉን ለመከላከል እና በድርጊቱ የተሳተፉ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያደርገውን ጥረት መደገፍ አለበት። ወንጀሉ በሚፈጸምበት ጊዜ ድርጊቱ የተፈፀመባቸው ግለሰቦች መረጃውን በሰዓቱ ለፖሊስ በማሳወቅ ወንጀለኞችን ተከታትሎ የመያዝ ጥረቱን አስቸጋሪ እንዳይሆን በማድረግ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል።

በጥቅሉ ሰዎችን አስገድዶ የመሰወር (Enforced Disappearance) ወንጀልን የመከላከል እና መቆጣጠር ተግባር የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ፣ ቁርጠኝነት እና የጋራ ርብርብ ይጠይቃል። የዕገታ ድርጊቱ በተደጋጋሚ የሚፈጸምባቸው አካባቢዎች ላይ ዘላቂ መፍትሔ መስጠት ይገባል።

# የሁለተኛ ትልውድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አስተባባሪነት በተዘጋጀው የጫካ ፕሮጀክት የአረንጓዴረ ዐሻራ መርሃ-ግብር ላይ ተሳትፈዋል። ከስዊድን ስቶክሆልም ከተማ ሁለት ልጆቻቸውን ይዘው የመጡት አቶ ተስፋዬ ይሰኛሉ በየካ ተራራ ላይ ችግኝ ሲተክሉ አግኝተናቸዋል።

ሁለተኛ ትውልድ ልጆቼን በአካባቢ ጥበቃ አረንጓዴ ዐሻራ ላይ በመሳተፌ ደስታ ተሰምቶኛል፤ እነሱም የዚህ በጎ ተግባር አካል በመሆናቸው ሀገራቸው ላይ በቀጣይ ለሚያከናውኑት ሥራ ጅማሮ የሚሆንና በኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል ይላሉ።

ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ስለሀገራቸው ይበልጥ እንዲያውቁና እንዲቆረቆሩ ተመሳሳይ የንቅናቄ ሥራዎች ላይ በስፋት ማሳተፍ እንደሚገባ የተናገሩት አቶ ተስፋዬ፤ አረንጓዴ ዐሻራው በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ነገ ሀገራቸውን ተረካቢ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ የሚያደርግና የኃላፊነት ስሜታቸውን የሚጨምር ተግባር መሆኑን ነው ያስረዱት።

ውልደቱና ዕድገቱ በደቡብ አፍሪካ የሆነው ወጣት ዳግም ዳግማዊ በበኩሉ በቤተሰቦቹ ሀገር ኢትዮጵያ መጥቶ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ላይ በመሳተፉ ደስተኛ መሆኑን ነው የገለጸው።

ሀገሬ ከእኔ ምን ትፈልጋለች የሚለውን በተከልኩት ችግኝ ላይ አየዋለሁ ያለው ወጣቱ፤ ችግኝ በአግባቡ መትከልና ተንከባክበህ ማሳደግን ይጠይቃል። ሀገርም ልክ እንደዚሁ ድጋፍና የሁል ጊዜም ክትትልን ትፈልጋለች፤ እኔም በምችለው ሁሉ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ አደርጋለሁ ሲል ነው የተናገረው።

ከአሁኑ ስለሀገራቸው እንዲያውቁ የተደረጉ ሁለተኛ ትውልድ ዜጎች በቀጣይ ለሀገራቸው የሚችሉትን ሁሉ በጎ ነገር ለማድረግ ወደኋላ እንደማይሉ ያነሳው ዳግም፤ ቤተሰቦቹ ስለሀገሩ ታሪክ፣ ባህልና፣ እሴት ጠንቅቆ እንዲያውቅ እያስተማሩ እንዳሳደጉት ይናገራል።

በርካታ ወላጆችም በውጭ ሀገራት የተወለዱ ልጆቻቸውን ስለኢትዮጵያ ጠንቅቀው እንዲያውቁና ለሀገራቸው የአረንጓዴ ዐሻራ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች ጥቅም የሚሰጥ ተግባር ላይ እንዲሳተፉ ከአሁኑ ሊያዘጋጇቸው ይገባል ሲል ሃሳቡን ሰጥቷል።

ከእህቱ ጋር ለችግኝ ተከላው መምጣቱን አመላክቶ፤ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መጥተው በተለያዩ ዘርፎች መሰማራትና የአቅማቸውን ድጋፍ ለሀገራቸው ማድረግ አለባቸው ሲል መልዕክቱን አስተላልፏል።

ከሳዑዲ ሪያድ ከሦስት ወንድ ልጆቻቸውና ከባለቤታቸው ጋር ወደ ኢትዮጵያ የመጡት አቶ ለሜሳ ኃይሉ፤ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ የመሬት መራቆትን በመከላከል የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅና የደን ሽፋን እንዲጨምር ያግዛል፤ ለዚህም ከነቤተሰቤ መጥቼ ተሳትፌያለሁ ይላሉ።

የሁለተኛ ትውልድ የሆኑ ልጆቼን ይዤ መምጣቴ ስለሀገራቸው ይበልጥ እንዲያውቁና ምን እየተደረገ ነው የሚለውን እንዲገነዘቡ ይረዳል ያሉት አባት፤ ቀጣዩ ትውልድ የኢትዮጵያን መጻኢ እድል የሚወስኑ የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች ላይ በስፋት እንዲሳተፍ ማድረግና የሀገሩን ስሜት ማጎልበት ይገባል ሲሉ ያነሳሉ።

ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በያሉበት ብቻ ሳይሆን ወደ እናት ሀገራቸው መጥተው እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን መመልከትና ምን ጎሎናል ምንስ ያስፈልገናል የሚለውን በመለየት የበኩላቸውን ለመወጣት ሊዘጋጁ ይገባል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ‹‹ሁለንተናዊ ብልጽግናን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እእንዲሁም በጎ የሥራ ባህል ግንባታ ላይ የተጀመሩ ሥራዎች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውንም አመልክተዋል።

ሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሲቋቋም ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው ያሉት ምክትል አፈ ጉባዔዋ፤ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚው ውስጥ የሚታየውን የሠለጠነና በክህሎቱ የበቃ የሰው ሃይል ችግር በመለየት በሚፈለገው ደረጃ ለመቅረፍ የሚያስችል የክህሎት ሥልጠና ክፍተትን መሙላት ቀዳሚው መሆኑን ተናግረዋል።

የሥራ ዕድል ፈጠራን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መፍታትና ሰላማዊ የኢንዱስትሪ ግንኙነትን ከመፍጠር አኳያ የነበሩትን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችል ደረጃ በበላይነት እንዲመራ እና እንዲያስተባብር ታሳቢ ተደርጎ ነውም ብለዋል።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሱን በማቋቋምና በማደራጀት ተጨባጭና ተስፋ ሰጪ ሥራዎችን በማከናወን በከፍተኛ ደረጃ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ተናግረዋል።

የሥራ እድል ፈጠራ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዕድገት መሰረት ነው ያሉት ምክትል አፈጉባዔዋ፤ መንግሥት ይህንን ታሳቢ በማድረግ ተቋሙ ክህሎት መር የሆነ የሥራ ዕድል ፈጠራ አቅጣጫን ተግባራዊ እንዲያደርግ አስፈላጊውን የሕግ ማእቀፍና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን እያደረገ እንደሚገኝ ወይዘሮ ሎሚ ጠቁመዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው የሥራ እድል ፈጠራ ሥራ ከኢኮኖሚ እድገት ጋር የተሳሰረ፣ ክህሎት መር እንደሆነም ጠቁመዋል።

ሙብትና ግዴታውን ያወቀ ምርታማነትን ማእከል ያደረገ አዲስ የኢንዱስትሪ ባህል ግንባታ እውን እየሆነ መምጣቱን ጠቁመዋል። የፈጠራ ሃሳብና ከፍተኛ የማደግ ፍላጎት ያላቸው ዘርፎች ላይ ትኩረት ተደርጓል።

ደጋፊ የሆነ፣ በቂ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ የሚያስችል ተኪ ምርት ላይ ትኩረት ያደረገ የሰው ኃይል ያስፈልጋል ብለዋል። የየአካባቢ ጸጋዎችን አልምቶ የመጠቀም ብቃት እንዲዳብር ክህሎቱ የዳበረ የሰው ኃይል ማፍራት ትኩረት እንደተደረገበትም አመልክተዋል።

የክህሎት ልማት ሥልጠና በፍላጎት መር አጫጭር ሥልጠና ላይ ያተኮረ እንዲሆን ዝግጅት መደረጉን፣ በኢንዱስትሪዎች ፍላጎትና በሠለጠነው የሰው ኃይል መካከል ትስስር ለመፍጠር ጥረት ሲደረግ መቆየቱን፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ወደ ተሟላ የዲጂታል አሠራር ለማሸጋገርና በራሳቸው አቅም የሚተዳደሩ ነጻ ተቋማትን ለመገንባት እየተሠራ እንደሚገኝም ነው ያብራሩት።

የዲጂታል አሠራሩን በ100 ፖሊ. ቴክኒክ ኮሌጆች ለመተግበር አቅጣጫ መቀመጡንና ኮሌጆቹ በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሁም በአካባቢዎች የሚገኙ ፀጋዎችን ታሳቢ ያደረጉና በእሴት ሰንሰለት ላይ የተመሠረቱ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ትኩረት እንደሚደረግም ጠቁመዋል።

ለትግበራው ደግሞ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር በጠንካራ ቁመና ላይ መገኘት አለበት ይህንኑ ታሳቢ ያደረ የሪፎርም ሥራ ሠርቷልም ሲሉ ተናግረዋል።

ግብርና፣ ኢንዱስትሪና ሌሎቹም ዘርፎች ተወዳዳሪ መሆን እንዲችሉ ተቋማችን በብቃትና በውጤታማነት ይቀጥላል ነው ያሉት።

# የገንዘብ ፖሊሲው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባንኮች ሊኩዲቲ (የገንዘብ እጥረት) ችግር ስላለባቸው ያንን ለማስተካከል ያስችላልም ነው ያሉት። እንደ ክቡር ገለጻ፤ አንዳንድ ባንኮች የመንግሥት ድጋፍ ባይኖራቸው ኖሮ ከስረው ሊዘጉ ይችሉ ነበር። ነገር ግን ጥንቃቄ የተላበሰ፣ ሥርዓቱን የጠበቀ አሠራር በመኖሩ በኢትዮጵያ ባንኮች በመንግሥት ድጋፍ ጭምር ሊቀጥሉ ችለዋል።

ይፋ የሆነው አሠራር ከዚህ በፊትም ሊኖር ይገባ የነበረ፣ ባንኮች እርስ በእርስ እንዲበዳደሩ የሚያስችል አሠራር የፈጠረላቸው ነው።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በርሄ ተስፋ (ዶ/ር) እንደሚሉትም፤ የባንክ ተመን የፖሊሲ አቋም ለመጠቆም፣ ሰፋ ያለ የገንዘብና የብድር ሁኔታዎች ላይ ተጽእኖ ለማድረግ ያግዛል።

ወለዶች ከፍ እያሉ በሄዱ ቁጥር አበዳሪዎች፣ ተበዳሪዎችና ባለሀብቶች ለውጦቹን በቅርበት መከታታል ይጠበቅባቸዋል። እያደገ ያለውን የገበያ ሁኔታ በመገንዘብ ስልቶቻቸውን ማስተካከል ይኖርባቸዋልም ይላሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ክቡር፤ የወለድ አከፋፈል ለባንኮች ዝቅ ቢልም ባንኮች በ17፣ በ18 እና በ19 በመቶ ወለድ ምጣኔ ማበደራቸው አይቀርም፤ በኢትዮጵያ ግሽበቱን ዝቅ ማድረግ እስካልተቻለ ተበድሮ ሥራ ለመሥራት የሚፈልገው ባለሀብት ለመሥራት ያዳግተዋል ይላሉ።

በውሳኔው የሀገር ውስጥ ባንኮች ተጠቃሚ ይሆናሉ የሚሉት ባለሙያው፤ ገንዘብ ባነሳቸው ቁጥር ግልጽ በሆነ መንገድ የሚሄዱበት፣ በጨረታ ተወዳድረውም ገንዘብ የሚያገኙበት መንገድ በአዲሱ ፖሊሲ እንደተመቻቸም ነው የሚጠቅሱት።

ሂደቱ የዘመናዊ ባንኮች አካሄድ በመሆኑ ዓለምአቀፍ ባንኮች ሀገር ውስጥ ገብተው በሚያጠኑበት ጊዜ እነዚህ አሠራሮች መኖራቸው የበለጠ ዋስትና እንደሚሰጣቸውም ክቡር ይናገራሉ።

የባንኩ ገዢ አቶ ማሞ፤ ከውሳኔዎቹ መካከል ለባንኮች የአንድ ቀን የብድርና የተቀማጭ ገንዘብ አገልግሎቶቹ ባንኮች በአንድ ቀን ውስጥ የገንዘብ አቋማቸውን ለማስተካከል እንዲረዳቸው ታሳቢ የተደረገ መሆኑን ይናገራሉ።

ባንኮች እርስ በእርስ የሚበዳደሩበትን የተነቃቃ የገንዘብ ገበያ ለመመስረት የሚያስችል የኤሌክትሮኒክ ግብይት ሥርዓት በቅርቡ ለመዘርጋት ዝግጅት ያጠናቀቀበት ውሳኔም ሲተገበር ትርፍ ገንዘብ ያላቸው የገንዘብ እጥረት ላጋጠማቸው ባንኮች ማበደር እንደሚችሉም አቶ ማሞ ይናገራሉ።

እርስ በርስ ብድር መውሰድ በባንኮች የተለመደ አሠራር ነው። በተጀመረው አሠራር ባንኮች ለአንድ ቀን ከሌላ ባንክ ይበደራሉ ወይም ደግሞ ራሱ ብሔራዊ ባንክ ያበድራቸዋል።

ከእዛ በላይ ደግሞ የተወሰኑ ቀናት የሚያስፈልግ ከሆነም እርስ በእርስ ብድር የሚወስዱበት ሥርዓት ክፍት ሆኗል። ይህ ጅማሮም የባንክን አሠራር ወደ ዘመናዊነት ይቀይረዋል ይላሉ ክቡር ።

ብሔራዊ ባንክ መጨውን ጊዜ የሚመጥን የማስተዳደር ከፍተኛ ክህሎት ሊያሳድግ ይገባዋል የሚሉት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)፤ በዓለም የፋይናንስ ሥርዓት በየሰከንዱ ከትሪሊዮን ዶላር በላይ በኢንተርኔት ይሸጋገራል። ይህንን ተከትሎም ነው የሀገር ኢኮኖሚ ሊያድግ የሚችለው።

ሁሉም ማዕከላዊ ባንኮች ተጠቃሚ እንደመሆናቸው ተጎጂም ሊሆኑ ስለሚችሉ የአስተዳደር ክህሎታቸውን ማሳደግ አለባቸው ፤ማሻሻያዎቹም ይህንን ታሳቢ ያደረጉ ናቸው።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፖሊሲ ነክ የወለድ ምጣኔ ለመጀመሪያ ጊዜ 15 በመቶ ተደርጓል፤ ቀላል ማበደሪያ አይደለም፣ ከፍተኛ ነው የሚሉት ክቡር፤ ባንኮች የሚያበድሩት ከእዛ በላይ ነው ቀንሰን እናበድር የሚል እሳቤን ይዟል፣ ነገር ግን ባንኮች በሚያበድሩበት ጊዜም ከተበዳሪው ወለድ ይጠይቃሉ።

ዛሬ አንድ ድርጅት ሥራ ከፍቶ 20 እና 30 በመቶ አትርፎ 15 በመቶ ለባንክ እዳውን ከፍሎ ያዋጣኛል ብሎ ለመቀጠል ያስቸግራል። ሆኖም ግን እንደእኛ አይነት ሀገር ላይ ይደረጋል። አፍሪካ ውስጥም ወለዳቸው በጣም ከፍተኛ የሆነበት ምክንያት ግሽበቱ ከፍተኛ በመሆኑ ነው። ከኢትዮጵያ ጋር ሲነጻጸር ዝቅ ያለ ነው ብለን ልንገምት እንችላለን።

የብሔራዊ ባንኩ ፖሊሲ ነክ የወለድ ምጣኔ ለመጀመሪያ ጊዜ 15 በመቶ ይሆናል። ተመኑ አሁን የሚታዩ ማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታዎችንና በከፍተኛ ደረጃ እየወረደ የመጣውን የባንክ ብድር እድገት ግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

ባንኮች በውድድር ላይ ተመሥርተው ለደንበኞቻቸው በሚሰጡት ብድር ላይ የሚያስከፍሉትን የወለድ መጠን በራሳቸው መወሰናቸውን እንደሚቀጥሉ፣ ባንኮች በቁጠባ ገንዘብ ላይ የሚከፍሉት ዝቅተኛ የሰባት በመቶ ወለድ በፖሊሲ ተመኑ ምክንያት ለውጥ እንደማይደረግበትም አቶ ማሞ ያመለክታሉ።

ከገንዘብ ፖሊሲ ጋር የተያያዙ ጨረታዎችን በየሁለት ሳምንቱ እንዲካሄድ የተደረሰው ውሳኔም ከዚህ በፊት ያልነበረ፣ ባንኮች በተለያየ መንገድ የሚያጋጥማቸው የገንዘብ እጥረት ለመሸፈን የሚረዳቸው አሠራር መሆኑን ክቡር ይጠቁማሉ።

አቶ ማሞ ለባንኮቹ ተጨማሪ ገንዘብ ለማቅረብ የሰነዶች ግብይትን ይጠቀማልም ብለዋል።

ቻይና በኢኮኖሚ በአንዴ የተመነደገችው እ.አ.አ በ2001 የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ከሆነች በኋላ የውጭ ባንኮችን አስገብታ ነው። የሀገር ውስጥ ባንኮች እንዲያድጉ የውጭ ባንኮች ቅርንጫፍ መክፈት እንዳይችሉ፣ ከሕዝቡ የቁጠባ ሂሳብ መሰብሰብም እንዳይፈቀድላቸው ገድባ እንደነበር ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ያነሳሉ።

የውጭ ባንኮች ሲመጡ ገንዘብ፣ ዓለም አቀፍ ተሞክሮ፣ ከፍተኛ የሥራ ልምድ፣ ዘመኑ የደረሰበትን የፋይናንስ ቴክኖሎጂ ይዘው ይመጣሉ። በፖሊሲው የውጭ ባንኮች የተወሰነ ሼር ከሀገር ውስጥ ባንኮች እንዲገዙ ስለሚፈቅድ የሀገር ውስጥ ባንኮችም አብረው ያድጋሉ።

እንደቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ፖሊሲዎቹ በኢኮኖሚ አስተዳደር ላይ መተማመንን ይፈጥራሉ። ብሔራዊ ባንክ ካፒታሉን ከፍ እያደረገ መሄዱ አይቀርም። የሀገር ውስጥ ባንኮች አሁን ሰብሰብ ማለት ይጠበቅባቸዋል።

የትላልቅ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ መግባት ለባለሀብቶች መተማመንን ይፈጥራሉ። በሀገር ውስጥ ሰላምና የኢኮኖሚ አስተዳደር ከሰፈነ ኢኮኖሚውን በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል።

የሀገር ወስጥ ባንኮችም በከፍተኛ ደረጃ ሊያድጉ የሚችልበት አጋጣሚ ስለሚፈጥር ባንኮቹ በመደራጀት ዓለም አቀፍ ባንክ ደረጃን በማሟላት መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ሃሳባቸውን አካፍለዋል።

እያንዳንዱ የባንክ ሠራተኛ በዘፈቀደ መረጃ አይቶ ለሌላ አካል የሚያስተላልፍ ከሆነ ተአማኒነት ስለሚጠፋ ባንኮች ጠንካራ መታመንን መገንባት አለባቸው ነው ያሉት ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር)።

ባለሙያዎቹ በማጠቃለያነት ርምጃው የሀገር ውስጥ ባንኮችን ተወዳዳሪ ያደርጋል፣ በኢትዮጵያ የባንክ አሠራር ቅልጥፍናን የተላበሰና የዘመነ እንዲሆን ያስችላል የሚለውን በጋራ ይስማሙበታል።

# በተሰበሰበው ገቢ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንዳሉት፤ ከተማችን የዓለም ዲፕሎማሲ ማዕከልነቷ የሚመጥን ይዘት እንዲኖራት ከሕዝባችን በተሰበሰበ ገቢ በርካታ የልማት ፕሮጀክቶችን እየሠራን ነው። ባለፈው በጀት ዓመት ከግብር ከፋዮች በተሰበሰበው ገቢ የከተማዋን ነዋሪዎች የኑሮ ጫና የሚያቃልሉ እና የከተማዋን ገጽታ የቀየሩ 18 ሺህ 091 የልማት ፕሮጀክቶችን ተሠርተዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት የሰበሰብነውን 146 ቢሊዮን ብር ከብክነት ጠብቀን የሕዝቡን የኑሮ ጫና የሚያቃልሉ እና የከተማችንን ገጽታ የቀየሩ በጠቅላላ 18 ሺህ 091 ፕሮጀክቶችን ሰርተናል ያሉት ከንቲባዋ፤ፕሮጀክቶቹ መጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረጉ፣ ከተማዋን ዘመናዊና ውብ ያደረጉ ናቸው ብለዋል።

የኑሮ ውድነት የሚያቃልሉ የገበያ ማዕከላት ፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ህንፃ እና የኮሪደር ልማት ከግብር በተሰበሰበው ገቢ መሠራታቸውንም በአብነት ጠቅሰዋል ።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ግብር ከፋዮቻችን በታማኝነት የሰጡንን ገንዘብ በታማኝነት በሚገባው የልማት ሥራዎች ላይ አውለናል ሲሉም ገልጸዋል።

ለገቢ ቤተሰቦቻችን ሁሉ፤ ከተማችን የምታመነጨው የገቢ አቅም ከዚህ በላይ መሰብሰብ እንደምንችል የሚያሳይ በመሆኑ ከብክነት፣ ከብልሹ አሠራርና ከሙስና በጸዳ መንገድ በ2017 በጀት ዓመት ያቀድነውን 230 ቢሊዮን ብር ገቢ በመሰብሰብ በጋራ እናሳካ ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

በዚህ ዓመት ለተገልጋዮቻችን ክብር ስንል የአገልግሎት መስጫዎቻችን እና የአሠራር ሥርዓታችን ላይ ማሻሻያዎችን ለማድረግ ሥራዎች ትኩረት ሰጥተን የምንሰራ ይሆናል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በ2016 በገቢ አሰባሰብ የተሳተፉ እና ለውጤታማነቱ አስተዋፅኦ ያበረከቱ አካላትን ሁሉ ያመሰገኑት ከንቲባ አዳነች፤ በ2017 በጀት ዓመት ለመሰብሰብ የታቀደው የ230 ቢሊዮን ብር ገቢ እንዲሳካም አደራ ብለዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# ይበል የሚያስብለው የብሔራዊ ባንክ ርምጃ፤

መንግሥት የዋጋ ግሽበቱንና እሱን ተከትሎ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ነው።በፍላጎትንና አቅርቦትን ለማመጣጠን ምርትንና ምርታማነት ለማሻሻል የግብርና ሜካናዜሽን፣ ኩታ ገጠም ግብርናን፣ በመስኖ በመታገዝ በዓመት ሦስት ጊዜ ለማምረት፣ እንዲሁም በሌማት ትሩፋት ጥረት እያደረገ ነው። በዚህም ይበል የሚያሰኝ የምርት እድገት የታየ ቢሆንም፣ የግብይት ሥርዓቱ ውስጥ ያለ ትብታብ አመድ አፋሽ እያደረገው ይገኛል።

ይሄንንም ችግር ለመሻገር በሚል፣ ለአብነት በአዲስ አበባ አምራቹንና ሸማቹን በቀጥታ ለማገናኘት የገበያ ማዕከላትን በሁሉም የመዲናዋ መግቢያዎች በመገንባት፤ ለሸማች ሕብረት ሥራ ማህበራት ተዘዋዋሪ ፈንድ በማቅረብ እንዲሁም የሰንበት ገበያዎችን በማበረታታት ገበያውን ለማረጋጋት ጥረት ተደርጓል። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ የፊስካልና የሞኒተሪ ወይም የገንዘብ ፖሊሲውን ለመቃኘት ማሻሻያዎች እየተደረጉ ይገኛል።

ከፊስካል ፖሊሲ አንጻር መንግሥት ዕቅዱን፣ በጀቱን ወይም ገቢና ወጪውን የዋጋ ግሽበቱን ከማረጋጋት አኳያ ሲቃኝ፤ በኢኮኖሚው ውስጥ የገንዘብ ዝውውሩን፣ ስርጭቱን፣ መጠኑን፣ የውጭ ምንዛሬን ምንዛሬን በመተመን የገንዘብ ወይም የሞኒተሪ ፖሊሲውን ያሻሽላል። ይሄንን ለመረዳት ሰሞኑን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይፋ ያደረገውን የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያ አዋጅ እንቃኝ።

አዲሱ የብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ ከአሥር ወራት ቀደም ብሎ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ የዋጋ ንረት ላለፉት በርካታ ዓመታት በኢትዮጵያ ከባድ የማክሮ ኢኮኖሚ ፈተና ሆኖ መቆየቱን አምነዋል። «ባለፉት አሥር ዓመታት የዋጋ ንረት በአማካይ ከ16 በመቶ በላይ ዕድገት አሳይቷል። ባለፉት ሁለት ዓመታት ደግሞ በአማካይ ከ30 በመቶ በላይ ዕድገት አሳይቷል። የዋጋ ንረት በደሃው የኅብረተሰብ ክፍል የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ ብዙ ጉዳት አለው። የዋጋ ንረት ለረዥም ጊዜ በቆየ ቁጥር አሁን በኢትዮጵያ እንደሆነው ሥር የሰደደ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥጋት ይፈጥራል። የዋጋ ንረት ይኖራል የሚለው ሥጋት በራሱ ለዋጋ ንረት መባባስ ምክንያት ይሆናል» ሲሉ በዚያ መግለጫ ተናግረው ነበር።

በወቅቱም፣ የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ጥብቅ የፊስካልና የሞኒተሪ ፖሊሲ ዕርምጃ እንደሚወሰድ ቃል ገብተው ነበር። ከአምስት ወራት ቀደም ብሎ ደግሞ ከብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያው ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ባንኩ የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር ዋና ትኩረቱ አድርጎ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ በዚህም በስድስት ወራት ውስጥ የዋጋ ንረት ምጣኔ ላይ አንፃራዊ ቅናሽ መመዝገቡን ተናግረው ነበር።

በዚህ ዙሪያ የተለያዩ ዘገባዎች እንዳመለከቱት፤ በወቅቱ ገዢው፣ «በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን የብድር ዕድገት በ14 በመቶ ገተነዋል። ብሔራዊ ባንክ ለመንግሥት የሚሰጠውን የቀጥታ ብድርም በ75 በመቶ ቀንሰነዋል። ባንኮች ወደ እኛ ለብድር ሲመጡ የምናስከፍለውን ወለድ ምጣኔ ወደ 18 በመቶ አሳድገነዋል። የገንዘብ ሚኒስቴርም ጥብቅ የፊስካልና የሞኒተሪ ፖሊሲ መከተል ጀምሯል። የመንግሥት የሀብት አጠቃቀምን ከብክነት በፀዳ መንገድ ለመምራት የሚያስችሉ ጥብቅ አሠራሮች ተዘርግተዋል፤» ሲሉ የተናገሩ ሲሆን፤ ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር በወሬ ሳይሆን ተጨባጭ ዕርምጃ መውሰድ መጀመሩን አስረድተው ነበር።

ይሁን እንጂ እሳቸውም ሆኑ መንግሥት የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ተጨባጭ ዕርምጃዎችን መውሰድ ስለመጀመራቸው ብዙ ቢናገሩም፣ ነገር ግን እስካሁንም የኢትዮጵያን ገበያ ከፍተኛ የዋጋ ንረት ተጭኖት ይገኛል። በመሆኑም ይሄንን እውነት በመገንዘብ እና የተነገረውን ቃል ለመፈጸም ብሔራዊ ባንክ በቅርቡ ባወጣቸው አዳዲስ አዋጆችና የአሠራር ማሻሻያዎቹ የዋጋ ንረቱን በመሠረታዊነት የሚፈቱ ዕርምጃዎችን አካቶ ማቅረቡ ትልቅ ዕርምጃ ነው።

በተለይ አዲሱ የብሔራዊ ባንክ ማሻሻያ አዋጅ ከዚህ ቀደም ለረዥም ዓመታት ሲሠራበት የቆየና ለዋጋ ንረት ዋና መነሻ ነበር። በመሆኑም በቆየው አሠራር ላይ ጠበቅ ያለ የማሻሻያ ድንጋጌ ይዞ መቅረቡ የሚያስመሰግነው ነው።

በዚህ ረገድ የብሔራዊ ባንክ ግብ የፋይናንስና የዋጋ ንረትን ማረጋጋት እንደሆነ በመጥቀስ የሚንደረደረው አዲሱ ረቂቅ አዋጅ፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጡ አዋጆችም ይህንኑ ግብ ለማሳካት በሚያስችል መንገድ በየጊዜው ማሻሻያ ሲደረግባቸው መቆየቱን ያትታል። ብሔራዊ ባንክን መጀመሪያ ያቋቋመው ቻርተር ቁ.30/1955 ከወጣ በኋላ በ1955፣ በ1968፣ በ1986 እና በ2000 የወጡ የገንዘብና የባንክ አዋጆች መኖራቸውን ይጠቅሳል።

እነዚህ አዋጆች የወጡባቸው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዐውዶች የተለያዩ ቢሆንም፣ ለብሔራዊ ባንክ ቁልፍ ሚናና ተቋማዊ ህልውና ዕውቅና የሰጡ እንደነበሩ ይጠቁማል። የብሔራዊ ባንክን ሥልጣንና ኃላፊነት፣ የባንኩን አስተዳደር፣ ባንኩ ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋር የሚኖረውን ግንኙነትንም የሚወስኑ ሕጋዊ ማዕቀፎችን በግልጽ ያብራሩና ያስቀመጡ፣ የባንኩን ካፒታል ያሳደጉ እንደነበሩም ይገልጻል።

እነዚህ አዋጆች ብሔራዊ ባንኩ ከመንግሥት ጋር የነበረውን ግንኙነት በምን መንገድ እንደወሰኑ አንድ በአንድ ያብራራል። በ1955 ዓ.ም. የወጣው የገንዘብና የባንክ አዋጅ ባንኩ ከመንግሥት ጋር ያለውን ግንኙነት ሲዘረዝር፣ ባንኩ ለመንግሥት የሚሰጠው ቀጥታ ብድር መጠን መንግሥት ባለፈው ዓመት ከሰበሰበው ገቢ 15 በመቶ እንዳይበልጥ የሚያስገድድ ሲሆን፤ በብድሩ ላይ ከሦስት በመቶ ያልበለጠ ዓመታዊ ወለድ እንደሚከፈልበትና ብድሩ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በስድስት ወራት ውስጥ መከፈል እንዳለበት ይደነግጋል።

አዲሱ ረቂቅ አዋጅ ማብራሪያውን ሲቀጥልም፣ በ1968 ዓ.ም. የወጣው የገንዘብና የባንክ ሥርዓት ቁጥጥር አዋጅ በበኩሉ፣ መንግሥት ከባንኩ የሚወስደውን የብድር መጠን ካለፈው በጀት ዓመት ገቢ ከ25 በመቶ እንዳይበልጥ ከማድረግ ውጪ፤ የወለድ ተመኑም ሆነ የብድር መመለሻ ጊዜው ከ1963 ዓ.ም አዋጅ ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን አድርጎታል ይላል። የ1963 ዓ.ም. ያለውን አዋጅ ይዘት ግን ሳይዘረዝር ነው ያለፈው።

ቀጥሎ የሚያነሳው በ1986 ዓ.ም. የወጣው የገንዘብና የባንክ አዋጅም ከብሔራዊ ባንክ የሚለቀቀው የቀጥታ ብድር መጠን መንግሥት ባለፉት ሦስት ዓመታት ከሰበሰበው አማካይ ገቢ ከ15 በመቶ እንደማይበልጥ፣ ብድሩም በቀጣይ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተከፍሎ ማለቅ እንዳለበት፣ ወለዱንም ባንኩ በገበያ ዋጋ እንደሚወስን ያስቀመጠ እንደሆነ ረቂቅ አዋጁ ያመለክታል።

ቀጥሎ የመጣው ያለው አዋጅ ቁጥር 591/2000 ግን፣ ቀደም ሲል የወጡ አዋጆችን ያሻሻለ ሲሆን፣ የመንግሥትና የብሔራዊ ባንክ የብድር ግንኙነት ገደብ ባለው መንገድ እንዳይመራ ያደረገ መሆኑን በግልጽ ይጠቁማል።

> **ብሔራዊ ባንኩ በአዲሱ አዋጁ የመንግሥት የሦስት ዓመታትን ጥቅል የኢኮኖሚ ገቢ አይቼ ነው የዚያን 15 በመቶ ብድር የምሰጠው፣ ይህም ተንከባላይ አይደለም፣ ብድሩን ሲከፍል ብቻ ነው ተጨማሪ ብድር መጠየቅ የሚችለው ማለቱ በእኔ ግምት ደፋርና ለውጥ የሚያመጣ ድንጋጌ ነው**

በ2000 ዓ.ም. የወጣው አዋጅ ባንኩ ለመንግሥትና ለፋይናንስ ተቋማት ብድር እንደሚሰጥ ከመግለጽ ውጪ ለመንግሥት በሚሰጠው ቀጥታ ብድር ላይ ግን ምንም ገደብ ሳይጥል በለሆሳስ ያለፈ የመጀመሪያው አዋጅ ነው ሲልም፣ አዲሱ የብሔራዊ ባንክ ማሻሻያ አዋጅ አስቀምጦታል። በመሆኑም ይህ በ2000 ዓ.ም. የወጣ አዋጅም ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ግሽበትን የሚቆጣጠርበትን አቅም ያዳከመ እንደነበር ጠቁሞ፣ አካሄዱ የዋጋ ንረትን አባባሽ መሆኑን ነው ያመለከተው።

ይህን ለመቀየር አዲስ የአዋጅ ማሻሻያ ማስፈለጉን የጠቆመው አዋጁ፣ በዚህም መሠረት፣ «በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 27 መሠረት ብሔራዊ ባንክ በጥሬ ገንዘብ ፍሰት ላይ የተመሠረተ ጊዜያዊ የአቨር ድራፍት አገልግሎት ከ12 ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተመላሽ የሚደረግ ብድር ለፌዴራል መንግሥት ሊሰጥ ይችላል። የብድር መጠኑም ካለፉት ሦስት የበጀት ዓመታት አማካይ ዓመታዊ የፌዴራል መንግሥት የሀገር ውስጥ ገቢ ከ15 በመቶ መብለጥ የለበትም» ሲል አዲስ የብድር ገደብ ደንግጎ አውጥቷል።

ይህ አዲስ የሕግ ማሻሻያ በኢትዮጵያ ያለቅጥ በተንሰራፋው የዋጋ ንረት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ ስለመሆኑ ማብራሪያ የተጠየቁት የቀድሞ ከፍተኛ የባንክ የሥራ ኃላፊ የሆኑት አቶ እሸቱ ታዬ፣ የብሔራዊ ባንክ አቋም እንደ ዜጋም ሆነ እንደ ፋይናንስ ባለሙያ በእጅጉ የሚያስደስት ሆኖ እንዳገኙት ነው የተናገሩት።

«ለረዥም ጊዜ ለመንግሥት በቀጥታም ሆነ ቀጥታ ባልሆነ መንገድ የሚሰጠው ብድር ገደብ እንዲበጅለት ሲጠየቅ ቆይቷል። ብሔራዊ ባንኩ በአዲሱ አዋጁ የመንግሥት የሦስት ዓመታትን ጥቅል የኢኮኖሚ ገቢ አይቼ ነው የዚያን 15 በመቶ ብድር የምሰጠው፣ ይህም ተንከባላይ አይደለም፣ ብድሩን ሲከፍል ብቻ ነው ተጨማሪ ብድር መጠየቅ የሚችለው ማለቱ በእኔ ግምት ደፋርና ለውጥ የሚያመጣ ድንጋጌ ነው፤» ሲሉ ባለሙያው ተናግረዋል።

የብሔራዊ ባንክ አዋጅ ባንኩ ከመንግሥት፣ ከባንኮች፣ ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮችና የፋይናንስ ተቋማት ጋር እንዲሁም ከግለሰቦች ጋር ጭምር የሚኖረውን ግንኙነት የሚወስን እንደሆነ የጠቆሙት አቶ እሸቱ፤ አዲሱ ሕግ በትክክል ከተተገበረ ትርጉም ያለው ለውጥ በዋጋ ንረት ላይ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

አያይዘውም፣ "የባንኮችን የብድር ጣሪያ ከ14 በመቶ በላይ እንዳይሆን ብሔራዊ ባንክ ክልከላ አድርጎ ነበር። ይህን ያደረገው ደግሞ የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር እንደነበር አስታውቋል። ባንኮችን ብድር ከልክሎ መንግሥት በሚበደረው ገንዘብ ላይ ገደብ ካላስቀመጠ ግን ለዋጋ ግሽበቱ መሠረታዊ አባባሽ ምክንያት የመንግሥት ብድር ነው ተብሎ ይፈረጃል። አሁን ግን በባንኮች በኩል ግለሰቦች በሚያገኙት ብድር ላይ ቁጥጥር ከማድረግ ጎን ለጎን በመንግሥት አበዳደር ላይም ቁጥጥር አድርጓል። ይህ በሁለቱም መንገድ በመንግሥትም በግለሰቦችም ተበዳሪነት ላይ ቁጥጥር የሚያደርግ ነው ማለት ነው። እስከ 2026 ባለው ዓመት ብሔራዊ ባንኩ የዋጋ ግሽበትን እስከ አሥር በመቶ ባለው አኃዝ ለማውረድ ያስቀመጠውን ግብ ለማሳካት ታስቦ የወጣ አዋጅ ይመስለኛል» በማለትም አቶ እሸቱ ሃሳባቸውን አክለዋል።

ብሔራዊ ባንክ፣ በአዲሱ አዋጅ የፌዴራል መንግሥት ከባንኩ የሚበደረውን ብድር መገደቡ በብዙዎች ዘንድ እየተደነቀ ቢሆንም፤ ከዚሁ ጎን ለጎን ግን ሥጋት የሚያነሱ ወገኖች አልጠፉም። ከእነዚህ አንዱ የሆኑት የኢኮኖሚ ተንታኙ አቶ ዋሲሁን በላይ አዲሱ አዋጅ መንግሥት ከብሔራዊ ባንክ ሊበደርባቸው የሚችልባቸው ምክንያቶች ተብለው የተዘረዘሩትን አመክንዮዎች ያጣቅሳሉ።

ለአብነትም፣ «መንግሥት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ማለትም ያልተጠበቀ የማኅበረሰብ ጤና፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ ድርቅ ወይም አግባብነት ያለውን ሕግ መሠረት አድርጎ የታወጀ አጠቃላይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና በፌዴራል መንግሥት ገቢ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ጉልህ የውጭ ኢኮኖሚ ለውጦች በተከሰቱ ጊዜ ይህን ጊዜያዊ ችግር ለመቅረፍ ሲባል፣ ብሔራዊ ባንክ ተጨማሪ ብድር ለመንግሥት የሚሰጥበትን አግባብ ደንግጓል» ተብሎ የተቀመጠውን ንዑስ ድንጋጌ የሚያወሱት አቶ ዋሲሁን፤ ኢትዮጵያ ደግሞ በእነዚህ ችግሮች ብዙ የምትፈተን እንደመሆኑም አዋጁ የመንግሥት ብድርን በሚመለከት ገደብ ካስቀመጠ በኋላ ይህን ሁሉ የመበደሪያ ቅድመ ሁኔታ መደርደሩ፣ በተጨባጭ የአዋጁ ገደብ ትርጉም ኖሮት እንዳይሠራ የሚያደርግ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

ይሁን እንጂ እንደ ሀገር አሁን ላይ ካለው ተጨባጭ እውነት እና የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው እያመጣ ካለው ውጤት አኳያ፤ ብሔራዊ ብንክ እንዲህ አይነት የገንዘብ ፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማድረጉ እጅጉን የሚያስመሰግነው ነው። ሆኖም በመልካም የሚነሱትን በማላቅ፣ በስጋት የሚጠቃቀሱትንም በማጤን ለፖሊሲው ተፈጻሚነትም ሆነ ውጤታማነት ሁሉም አካል የበኩሉን ሊወጣ ይገባዋል የሚለው መልዕክቴ ነው።

ሻሎም ! አሜን።

## የሕይወት ገጽታ

# ለ117ኛ ጊዜ ደም በመለገስ
# የበርካቶችን ሕይወት የታደገችው ነርስ

**አመለወርቅ ከበደ**

በዓለማችን ሆነ በሀገራችን በሚኖሩበት የሕይወት ዘመን በአጋጣሚ ወይም በራሳቸው ተነሳሽነት ሌሎችን የመርዳት ትልቅ ባህል ያላቸው በርካታ ግለሰቦች እንዳሉ አስረጂ አያስፈልገውም። በዛው ልክ ደግሞ ለመርዳት እና በጎ ነገር ለማድረግ አቅም ኖሯቸው በቸልተኝነት ወይም፣ በፍላጎት ማጣት ምክንያት ይህቺን ዓለም የሚሰናበቱ በርካቶችም እንደሆኑ እሙን ነው።

የሰው ልጅ እንደመሆናችን ሌሎችን ለመርዳት የግድ በሚሊዬን የሚቆጠር ብርና ወርቅ ያለን ሰዎች መሆን አይጠበቅብንም። ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው የሚል ዘመን የማይሽረው ብሂል እንዳለን ሁሉ፤ በተለያዩ መንገዶች ሌሎችን መርዳት እንድንችል ተፈጥሮ የለገሰችን ትልቅ ጸጋ አለ።

ደም መለገስ ደግሞ ተፈጥሮ ከቸረችን ስጦታዎች ሁሉ የማይቋረጥ ስጦታ ነው። ይህን የተፈጥሮ ስጦታ ተጠቅመው ለበርካታ ሰዎች ዳግም በሕይወት ለመኖር ምክንያት የሆኑት ሲስተር አሰጋሽ ጎሳ ደግሞ አንዷ ናቸው።

ሲስተር አሰጋሽ ጎሳ ይባላሉ። በኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ስለ ደም ልገሳ ትምህርትና ቅስቀሳ የሚሰጡ ባለሙያ ናቸው። ለወላጆቻቸው አራተኛ ልጅ ሲሆኑ ፤ትውልድ እና እድገታቸው በድሮ ስሙ አርሲ ክፍለ ሀገር አሰላ ከተማ ነው። የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁት በእዛው አሰላ ከተማ መሆኑንም ሲስተሯ ይገልጻሉ።

የትምህርት አቀባበላቸው መሀከለኛ ከሚባሉ ተማሪዎች መሆኑን የሚያስረዱት ሲስተር አሰጋሽ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት ወደ ነርሲግ ሙያ ለመግባት ሃሳብ ባይኖራቸውም በአካባቢያቸው አንዳንድ ሳቢ ምክንያቶች እንደነበሩ ያነሳሉ።

ወደ ነርሲግ ሙያ እንዴት እንደገቡ የሚናገሩት ሲስተር አሰጋሽ፤ በመጀመሪያ አባታቸው የጤና ባለሙያ በመሆን በጤና ተቋም እንደሚሰሩ በመግለጽ፤ በአቅራቢያቸው ጤና ተቋም ስለነበር እዛ የሚሰሩት ነርሶች የሚለብሱት ልብስን ሲመለከቱ የፈጠረባቸው ስሜት ወደ ነርስ ሙያ እንደተሳቡ ይናገራሉ።

በዚህ ሁኔታ የህክምና ባለሙያዎችን እያዩ ማደጋቸው ወደ ሙያው ለመግባት በአዕምሯቸው ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን የሚገልጹት የህክምና ባለሙያዋ፤ ወለጋ ነርሲንግ ኮሌጅ ገብተው ትምህርታቸውን እንደተከታተሉ ያስረዳሉ።

በዙሪያችን ያሉ ሰዎች በቀን ተቀን እንቅስቃሴያችን የምንመለከታቸው ተግባራት ወደ ከፉም ሆነ ወደ ደግነት እንድንገባ ተጽእኖ እንደሚያደርጉ ሁሉ፤ ሲስተር አሰጋሽም ወደ በጎ አድራጎት እንዲገቡ ትልቁን ሚና የተጫወቱት እናት እና አባታቸው ናቸው።

‹‹እናቴ ጾም በሚያዝበት ወቅት በአካባቢው ያሉ የጎረቤት ሴቶች ትረዳለች። ጾም በሚፈታበት ወቅትም ለጎረቤት ሴቶች ቅቤ ወስዳ ትቀባቸው ነበር። አባቴ ጎሳው ይባላል ጥሩ ስነ ምግባር ያለው አባት ነው። እድገቴ በእንደዚህ አይነት ቤተሰብ ውስጥ መሆኑ ተጽእኖ አሳድሮብኛል›› ይላሉ።

**ወደ ደም ልገሳ ተግባር የገቡበት መንገድ**

ወደ ደም ልገሳ ተግባር እንዲገቡ የገፋቸው በስራቸው አጋጣሚያ ያጋጠማቸው ክስተት እንደነበር የሚያስታውሱት ሲስተር አሰጋሽ፤ በደም ባንክ ውስጥ በሚሰሩበት ወቅት አንድ አባወራ ሚስቱ ታማ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ገብታ ስለነበር፤ ደም ስላስፈለጋት ለባለቤቱ በሚሰጣት ደም ምትክ ደም እንዲለገስ ተጠየቀ።

በዛን ወቅት አባወራው ከክፍለ ሀገር ስለመጣ የምትክ ደም ሊሰጥ የሚችል የቅርብ ዘመድ እንኳን በዙሪያው አልነበረም። ያ አባወራ በጣም ውጥረት ውስጥ ከመግባቱ የተነሳ ከሆስፒታሉ እየሮጠ ወደ ደም



**ሲስተር አሰጋሽ ጎሳ**

ባንክ ሲመጣ ደክሞት ስለነበር እያለከለ ነበር የመጣው። ሚስቴ፣ የልጆቼ እናት ልትሞትብኝ ነው ወይም እኔ ደም ልለግስና እሷ ኖራ እኔ ልሙት የሚል ተማጽኖ አሰማ። ሲስተር አሰጋሽ ውስጣቸው ተነካ።

የአባወራው ጭንቀት ውስጣቸው ገባ። ለሚስቱና ለቤተሰቡ ያለው ፍቅር እና እርሱ ሞቶም ቢሆን ባለቤቱን ለማዳን ሲያደርግ የነበረው ጥረት እስከዛሬ አይረሳቸውም። ‹‹ያ ሰው ደክሞት እያለከለከ ነው ወደ ደም ባንክ የደረሰው። በዛ ላይ ከክፍለ ሀገር ነው የመጣው። በዙሪያው ምንም ዘመድ ስለሌለው ምግብ እንኳን በልቶ ላይሆን ይችላል። ምናልባት ደሙን ይዞ ሲሄድ እራሱን ስቶ ሊወድቅ ይችላል ››የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ ይህ ሰው ደም እንዲለግስ ማድረግ ወንጀል ነው በማለት ይገልጻሉ።

ምናልባት ከተማ ውስጥ የሚኖር ሰው ቢሆን እሱ መለገስ ባይችል እንኳን በዙሪያ ያለ ሰው ወንድም ሆነ እህት ወይም ጎረቤት መጥቶ እንዲለግስ ማድረግ ይቻላል። ይህ ሰው ከገጠር ነው የመጣው፤ባለቤቱን የሚያስታምማት እሱ ብቻ ነው። እንዳጋጣሚ ሆኖ በወቅቱ በሥራ ቦታው ተረኛ የነበርኩት እኔ ነበርኩና በጣም ስላሳዘነኝ እኔ ልስጥ አልኩና ሰጠሁ። አባወራው የተጠየቀው ሁለት ዩውኒት ደም ስለነበር አንድ ዩኒት ደም ከራሳቸው በመለገስ አንዱን ዩኒት ደም ደግሞ ለማግኘት መፍትሄ መፈለግ ጀመሩ።

‹‹በዛን ወቅት ከቦታ ቦታ በመሄድ የደም ልገሳ ቅስቃሳ በማድረግ ደም የምንሰበስብ ስለሆነ አንዱን ዩኒት ደም እኔ ከሰጠሁት በኋላ፤ አንዱን ደግሞ በቅስቀሳ ወቅት ከሚሰበሰበው ደም እንደምተካ ነግሬ፤ሴትዮዋ ደም እንድታገኝ አደረግኩ›› ይላሉ።

**ሲስተር አሰጋሽ ደም መስገስ የጀመሩት ከ1984 ዓ.ም በደም ባንክ አገልግሎት ሥራ መሥራት ከጀመሩበት ሰሞን አንስቶ ሲሆን፤ አሁን ላይ ለ 117ተኛ ጊዜ ደም ለግሰዋል፡፡በ2010 ዓ.ም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 19ኛውን የጤና ጉባኤ በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ ባካሄደበት ወቅት፤ ለ66 ጊዜ ደም በመለገስ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የላቀ ተሸላሚ በማለት ሽልማት ሰጥቷቸዋል**

በወቅቱ በክፍያ ደም የሚለግሱ ሰዎች መኖራቸውን የሚናገሩት ባለሙያዋ‹‹ እኔ እሰጣለሁ ተቀማጭ ደም አለኝ››እያሉ ደም የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ለማስማማት የሚጥሩ እንዳሉም ያነሳሉ።

እነዛ ሰዎች የጤንነታቸው ሁኔታ ስለማይታወቅ አንድ ሰው ከነዛ ሰዎች ደም ከገዛ በኋላ ተቀባይነት የማይኖርበት አጋጣሚ ብዙ እንደሆነም ሲስተር አሰጋሽ ያስረዳሉ።

እናም በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ተቸግረው ሲመጡ ተረኛ ከሆኑ ደም የሚለግሱበት አጋጣሚ የበዛ እንደነበር ይናገራሉ። አንድ ሰው ደም የሚለግሰው የመጀመሪያውን ከለገሰ በኋላ ሦስት ወር ሲሞላው መሆኑንም ያስረዳሉ።

ነገር ግን እሳቸው በወቅቱ ኮምፒውተር ስላልነበር በሁለት ወር ውስጥ እንኳን የሚሰጡበት ሁኔታ ነበር። አሁን ኮምፒውተር ስላለ በኮምፒውተር ይመዘገባል። አንድ ሰው ደም ለግሶ ሦስት ወር ካልሞላው ኮምፒውተሩ አይቀበልም ሲሉ ያስረዳሉ።

‹‹የዛን ወቅት ሦስት ወር ሳይሞላኝ ደም የምለግስ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር ይመስገን ምንም አይነት ጉዳት አልደረሰብኝም። ደግሞም ደም በሚለገስበት ወቅት የደም መጠኔ፣ ክብደቴ ስለሚለካ እና ምርመራዎች ስለሚደረግልኝም ጉዳት አልደረሰብኝም›› ይላሉ።

‹‹ያ አባወራ ነው ደም እንድስጥ መነሻ የሆነኝ። ከዚህ በፊት የደም እጥረት አጋጥሞት ደም የለገስኩለት ዘመድም ሆነ ጓደኛ ስላልነበረኝ ለመጀመሪያ ጊዜ ደም የለገስኩት ለዛ አባወራ ሚስት ነው››የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ ለአባወራው ሚስት ደም ሲለግሱም ገና ደም ባንክ የተቀጠሩበት ወቅት እንደነበር ይናገራሉ።

‹‹የአባወራው ሚስት ምን ደረጃ እንደደረሰች አላወኩም። ምናልባት ጊዜ አጥቶ ይሁን፤ ወይም ማመስገን እንዳለበት ባለማወቅ ምክንያት ይሁን አባወራውም ተመልሶ መጥቶ የደረሰበትን ደረጃ አልነገረኝም። ነገር ግን እኔ በዋናነት የሚያስደስተኝ እኔ በለገስኩት ደም የሰው ሕይወት መትረፉ ነው›› በማለት ይገልጻሉ።

ሲስተር አሰጋሽ እንደሚሉት፤ አንድ ሰው ደም ተለግሶለት ሕይወቱ ተርፎ፤ ደምባንክ መጥቶ የማመስገን ልምድ የለም። አጋጥሟቸውም አያውቅም። ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ እንደ ሀገር ደም ለመለገስ ፍርሀት አለ። ይህንኑ ከግንዛቤ በማስገባት ሰዎች ደም እንዲለግሱ የቅስቀሳና የግንዛቤ ትምህርት እንደሚሰጡ ይናገራሉ።

በደም ባንክ የተለያዩ የደም አይነቶች አሉ የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ ሆስፒታሉ በሚጠይቀው የደም አይነት ደምባንክ ይሰጣል። በዛ ምትክ ነው በዙሪያው ያሉ ሰዎች እንዲለግሱ ይደረጋል። አንድ ሰው የደም እጥረት አጋጥሞት በዙሪያው ያሉ ሰዎች ደም እንዲለግሱ ሲደረግ፤ ተመሳሳይ እንዲሆን አይጠበቅበትም።

ሲስተር አሰጋሽ ደም መለገስ የጀመሩት ከ1984 ዓ.ም በደም ባንክ አገልግሎት ሥራ መሥራት ከጀመሩበት ሰሞን አንስቶ ሲሆን፤ አሁን ላይ ለ 117ተኛ ጊዜ ደም ለግሰዋል። በ2010 ዓ.ም የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 19ኛውን የጤና ጉባኤ በአማራ ክልል ጎንደር ከተማ ባካሄደበት ወቅት፤ ለ66 ጊዜ ደም በመለገስ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የላቀ ተሸላሚ በማለት ሽልማት ሰጥቷቸዋል።

በ2013 ዓ.ም የቀድሞ ጤና ሚኒስትር የነበሩት ዶክተር ሊያ ታደሰ ሲስተር አሰጋሽ ለ80 ጊዜ ደም በመለገስ በሴት ደም ለጋሾች መሃከል ክብረወሰን ማስመዝገባቸውን አስመልክቶ የምስጋና እና የእንኳን ደስ አለሽ መልእክት አስተላልፈው ነበር።

**ሌሎች የበጎ አድራጎት ሥራዎች**

በኢትዮጵያ ደምና ህብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ለ117ኛ ጊዜ ደም በመለገስ...

ከገጽ 6 የዞረ

በተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር ህብረተሰቡ ደም እንዲለግስ የግንዛቤ ትምህርት መስጠት እና ሰዎች ደም እንዲለግሱ የንቅናቄ ሥራ ይሠራሉ። ሌላው በስፋት ደም ሊለግሱ የሚችሉ አካባቢዎች በመለየት ደም እንዲለግሱ የማድረግ ሥራ ይሠራሉ።

‹‹ ደም ከመለገስ ውጪ በተለያዩ አጋጣሚዎች በመንገድ ስንቀሳቀስ እኔ ወደምሄድበት አቅጣጫ እቃ ተሸክመው የሚሄዱ አቅመ ደካሞችን ስመለከት የያዙትን እቃ በመሸከም እረዳቸዋሉ›› ይላሉ። የበጎ አድራጎት ሥራቸው በዚሁ አልተገደበም። በሚኖሩበት አካባቢ አንዳንዴ ለተቸገሩ ግለሰቦች ልብስ እና ገንዘብ በመስጠት የሚረዱ መሆኑንም ያነሳሉ።

አንድ ሰው በአንድ ጊዜ የሚለግሰው ደም በደም እጥረት ለተቸገሩ ለሦስት ሰዎች ያገለግላል። አንድ ደም የሚለግስ ሰው ምንም እንከን ሳይገጥመው በተወሰኑ ደቂቃዎች ተነስቶ ወደ ሥራው ሊመለስ ይችላል። ነገር ግን ይህን ለማድረግ ችላ በመባሉ፤ በግንዛቤ እጥረት እና ፍረሃት በደም እጥረት ምክንያት በርካታ ሰዎች ይችን ምድር ዳግም ላለማየት ይሰናበታሉ።

ምናልባት እነዚህ ሰዎች የእነሱን እጅ የሚመለከት ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ሀገርን በእውቀታቸው የሚረዱ እና በበጎ ፈቃደኝነት የሚያሳድጉት ልጅ ሊኖር ይችላል። ቤተሰቦቻቸውን እና ሀገራቸውን ይረዳሉ ተብሎ ትልቅ ተስፋ የተጣለባቸውም ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ ግለሰቦች ሲቀጠፉ ቤተሰብ፣ ዘመድ፣ ጎረቤት ደረጃው እያደገ ሲመጣም ሀገር ይጎዳል። ‹‹ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ደም ስለግስ ነው የቆየሁት። እኔ አንዴ የምሰጠው አንድ ዩኒት ደም ለሦስት ሰዎች ያገለግላል። በዚህም ከእግዚአብሄር በታች የበርካታ ሰዎችን ሕይወት ማዳን ችያለው›› ሲሉ ያስረዳሉ።

መጠነኛ የደም መፍሰስ ላጋጣማቸው ‹‹ፕላዝማ ››፤ ለሚደሙ ደግሞ የሚደማውን ደም ለማቆም ‹‹ፕሌትሌት›› ይሰጣል። በተጨማሪም ቀይ የደም ሴል ለማያመርቱ የሚሰጥ ደም አለ ሲሉ ያስረዳሉ።

በዚህም ደም ልገሳ ተግባራቸው ለበርካቶች መድረሳቸውን የሚገልጹት ሲስተር አሰጋሽ፤ ‹‹አንዴ የሰጠሁት ደም ለሦስት ሰው የሚደርስ ከሆነ 117 ጊዜ የሰጠሁት ደም በርካቶችን መታደግ እንደቻለ በቀላሉ መረዳት ይቻላል›› ይላሉ።

አንድ ሰው ደም ሲለግስ ምርመራ ተደርጎለት በክብደቱ መጠን 350 ዩኒት ወይም 450 ዩኒት ነው የሚወሰደው። ከ350 ዩኒት በላይ የሚወሰድ ደም በሚለግሰው ግለሰብ ደም ውስጥ ጥሩ የአይረን መጠን ካለ ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

ደም ከሰውነታችን ሲወጣ ይረጋል። ደሙ ቀጣይ ለሚሰጠው ግለሰብ ጋር እስከሚደርስ ድረስ ነፍስ እንዲኖረው እና እንዳይረጋ የሚያደርግ ንጥረ ነገር ከደም ከረጢቱ ጋር አንድ ላይ ታሽጎ ይመጣል። ስለዚህ 350 ዩኒቱ ወይም 450 ዩኒቱ በሙሉ ደም አይደለም ሲሉ ያስረዳሉ።

## ደም መስገስ የሚያስከትለው ጉዳት ይኖር ይሆን ?

ደም መለገስ ጉዳት የለውም ሲሉ የሚያስረዱት ሲስተር አሰጋሽ፤ ደም በሰውነት ውስጥ አይጠራቀምም፤ከወራት በኋላ ይሞታል ፤በቦታው ሌላ ደም ይተካል። ‹‹እኛ ግን በምንለግሰው ደም የሦስት ሰዎችን ሕይወት እንታደጋለን›› ሲሉ ይናገራሉ።

በደም ውስጥ ያሉ ህዋሳት ስለሚሞቱ ደም ጊዜው ሲደርስ በሽንት እና በላብ የሚወገድ ነው። አብሯቸው ዘላለም የሚቀመጥ የሚመስላቸው ሰዎች እንዳሉም ይገልጻሉ።

የካንሰር ታማሚዎች፣ የመኪና አደጋ የገጠማቸው ፣ እናቶች እና ሎሎች በርካታ ደም የሚፈልጉ አካላት ስላሉ ሁልጊዜም ደም የሚለግሰው ሰው ማሰብ ያለበት እነሱን ከግምት ማስገባት አስፈላጊ ነገር መሆኑን ይመክራሉ።

‹‹በሕይወታችን ቆይታችን ምን እንደምንሆን አናውቅም። ስለዚህ በምድር ቆይታችን ከራሳችን አልፈን ለሌላ ሰው መኖር ትልቅ በጎ ተግባራ ነው ››ሲሉ ይናገራሉ።

“

**አንዳንዴ መርፌ**

**ፈርተው ደም የማይለግሱ ሰዎች አሉ። ‹‹ሰው ጦር ሜዳ ይሄድ የለ እንዴ›› የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ ‹‹እኛ ሰላም ወጥተን እንድንገባ አንድ ወታደር ነፍስ እስከመስጠት ከደረሰ በሰላም ሀገር ቁጬ ብለን ደም መለገስ ትልቅ ጉዳይ ሊሆንብን አይገባም››**

ደም መለገስ ደግሞ ሰው በመሆናችን ብቻ የምናደርገው በጎ ሥራ ነው የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ ስለዚህ ማንም ሰው እድሜው ከ18 እስከ 65 የሆነ፣ ክብደቱ ከ45 ኪሎ በላይ፣ሌላ የጤና ችግር የሌለበት እና የማታጠባ ሴት ከሆነች ደም መለግስ ይችላሉ ሲሉ ያስረዳሉ። በነገራች ላይ ከ18 እድሜ ክልል በላይ የሚባለው በሕገመንግሥቱ የተቀመጠውን አንድ ሰው በራሱ የመወሰን አቅም መሰረት በማድረግ ነው እንጂ የ16 እና 17 ልጅም በወላጆቹ ፈቃድ መለገስ ይችላል ይላሉ።

‹‹ደግሞ አንድ ሰው ደም ለመለገስ ሲመጣ የደም ግፊት ሆነ ሌላ በሽታ ካለበት ተመርምሮ ነው የሚሰጠው እንጂ ለመለገስ ስለመጣ ብቻ ደም እንዲለግስ አይደረግም ››ይላሉ።

‹‹ከደም ግፊት ጋር ተያይዞ የተሳሳተ ግንዛቤ አለ። ደም ግፊት ማለት ብዙ ደም አለን ማለት አይደለም። በአጋጣሚ በ2010 ዓ.ም በሰኔው ፍንዳታ ወቅት ደም ግፊት ስለነበረባቸው በተሳሳተ ግንዛቤ ብዙ ደም ነው ያለኝ በማለት ደም ለመለገስ አስበው አንድ ግለሰብ ከጋምቤላ ድረስ መጥተው ነበር። ነገር ግን የደም ግፊት ስለነበረባቸው መለገስ እንደማይቻል ተነግሯቸዋል›› ሲሉ ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

እኒህ ሰው‹‹ ኧረ እኔ ብዙ ደም አለኝ መለገስ እችላለው በማለት ከኛ ጋር በዙ ተከራከሩ። አይ የደም ግፊት በሽታ ስላለበዎት መለገስ አይችሉም ብለን ነገርናቸው። በመጨረሻም ሁኔታውን ተረድተው ወደ መጡበት ተመለሱ››ሲሉ አጫውተውናል።

ሲስተር አሰጋሽ እንደሚመክሩት ሰዎች ጤናማ በሆኑበት ወቅት ስለደም ልገሳ አውቀው ቢለግሱ መልካም ነው። ደግሞም ደም መለገስ ከድንገተኛ የልብ ህመም፣ ከአይረን ክምችት፣ ከስኳር እና ኮልስትሮል ይታደጋል ሲሉ ደም መለገስ የሚሰጠውን ጥቅም ያስረዳሉ።

አንድ ሰው የልብ ህምም ኖሮበት ተመርምሮ እስካላወቀ ዝምብሎ ማጅራቱን ያዘኝ እንዲህ አደረገኝ እያለ እቤቱ ይቀመጣል። ደም ለመለገስ አንድ ግለሰብ ሲመጣ እኛ የልብ አመታቱን እንመረምርና ችግር ካለ ሌላ ጊዜ እንዲመጣ እናደርጋለን ይላሉ ሲስተር አሰጋሽ።

ደም በሚለግሱበት ወቅት የደም አይነታቸውን፣ የኤች አይቪ፣ የጉበት እና የሌሎች በሽታዎች ምርመራ ተደርጎ ውጤት የሚነገር ስለሆነ ደም የሚለግሱ ሰዎች በዚህም ተጠቃሚ ይሆናሉ ሲሉ ይናገራሉ።

## ደም በመስገስ የተገኘ ጥቅም

ቀደም ሲል ደም የሚለግሱ ሰዎች ጥቂት ስለነበሩ በእይታ ብቻ ይታወቁ እንደነበር የሚናገሩት ሲስተር አሰጋሽ፤ በተደረጉልን የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አሁን በርካታ ሰዎች ደም በመለገስ ላይ እንደሚገኙ ይናገራሉ። ደም የምለግሰው በየሦስት ወር አንድ ጊዜ ሲሆን፤ በአንድ ዓመት አራት ጊዜ በመደበኛነት እለግሳለሁ ሲሉ ሲስተር አሰጋሽ ያስረዳሉ።

ደም መለገስ ከኮልስትሮል፣ ከድንገተኛ የልብ ህመም እና ሌሎች በሽታዎች ይታደጋል። ሲስተሯ ለረጅም ዓመታት ደም በመለገሳቸው ከእነዚህ በሽታዎች ነጻ ሊሆኑ ችለዋል። ከምንም በላይ ደግሞ ደም በመለገስ በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች ሕይወት መዳን ምክንያት በመሆናቸው፤ ከፍተኛ የህሊና እርካታ እንደሚሰማቸው ያስረዳሉ።

## ገጠመኞች

አንዳንዴ ደም ልገሳ ሲባል ዝምብሎ የሚቀዳ ወይም በፋብሪካ የሚመረት የሚመስላቸው አሉ። አንድ አባወራ ሚስታቸው በወሊድ ምክንያት ብዙ ደም ፈሷት ስለነበር፤ እሳቸው እንዲሰጡ ሲጠየቅ ‹‹ሁለታችንንም ልትገሉን ነው ወይ ልጆቼን ሌላ ሚስት አግብቼ አሳድጋቸዋለሁ›› ያሉትን አባት እንደማይረሷቸው ይገልጻሉ።

ሌላውኛው ገጠመኝ ደግሞ አንድ እናት ሁለት ዩኒት ደም ያስፈልጋቸዋል፤ አንደኛውን ሴት ልጃቸው እንድትሰጥ ሌላኛውን ደግሞ ወንድሟ እንዲሰጥ ተብሎ መጡ።

ወንዱ ለመስጠት በጣም ስለፈራ የደም ግፊቱ ጨመረ፤በጣም ተጨናነቀ። እንደዛ ሲሆን እህቱ ሁለተኛውን እኔ ጨምሬ ልስጥ አለችን። የሴቷ ጥንካሬ ያስደስታል። ብዙ ጊዜ ሴቶች ደም ለመለገስ የተሰጡ ይመስላል የሚሉት ነርሷ፤‹‹ ብዙ ጊዜ ወንዶች ሲጠየቁ ላስብበት፣ ዝግጁ አይደለሁም ይላሉ። ነገር ግን ሴቶች ወደያውኑ ነው የሚወስኑት›› ይላሉ።

ሌላኛውን አሳዛኝ ገጠመኛቸውን የሚናገሩት ሲስተር አሰጋሽ፤ አንድ አባት ሚስቱ ወለደችና ለተወለደው ሕፃን ደም መቀየር አስፈልጎ ስለነበር ሚስቱ አራስ ስለሆነች መስጠት ስለማትችል፤ አባትየው እንዲሰጥ ይጠየቃል ። ሰውየውም ይሄድና ወላጅ እናቱን ያማክራል። እናቱም የሚሞት ስለመሰላቸው ‹‹አንተ ብትኖር ሌላ ልጅ መውለድ ትችላለህ፤ደም መስጠት የለብህም ›› ብለው ስለመከሩት እሱም ሳይሰጥ ቀረ ። በኋላ ላይ ስንሰማ ልጁ ማረፉን ሰማን ይላሉ።

## አርአያነታቸውን የተከተሉ

‹‹የኔን አርአያ የተከተሉ ብዙዎች አሉ። ቤተሰቦቼ፣ እህቶቼ እና ሌሎች በርካታ ሰዎች ደም መለገስን እንደባህል የወሰዱ አሉ። ፎቶግራፎቼ ደም ባንክ ተሰቅለው ሲመለከት አንቺ ይህን ያህል ጊዜ እስከምትለግሺ እኔ የትነበርኩ ብሎ የተቆጨ እና ከዛ በኋላ በቋሚነት ደም በመለገስ ለበርካታ ጊዜ የለገሰ እና አሁንም እየለገሰ የሚገኝ ሰው አውቃለሁ›› ሲሉ ይናገራሉ።

የእሳቸውን አርአያነት በመከተል ለ92 ጊዜ ደም የለገሰ አለ። አርአያነታቸው በቤተሰብ ውስጥም ቀጥሏል። አንዲት ሴት ልጅ አለችኝ የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ እሷም በቅርቡ ለ14 ጊዜ ደም እንደለገሰች ይገልጻሉ።

## ደም የመስገስ ልምድ አሁን ላይ

ሲስተር አሰጋሽ እንደሚናገሩት አሁን ላይ ደም የመለገስ ተግባር በጣም እያደገ መጥቷል። በፊት ለዘመዳቸው እንኳን ደም ለመስጠት በጣም የሚያስቸግሩ ሰዎች አሁን ከራሳቸው አልፈው በበጎ ፈቃደኝነት ደም የሚለግሱ ሰዎች ብዙ ናቸው ሲሉ በማሳያነት ያነሳሉ።

ባህሉ እያደገ ቢመጣም አሁንም የደምና ህብረህዋስ ባንክ አገልግሎት የሚፈለገውን ያህል አልደረሰም። የዓለም ጤና ድርጅት ባወጣው ጥናት እንደሀገር የደም ለጋሾች ቁጥር ገና አንድ በመቶ እንኳ አልደረሰም ። በኢትዮጵያ 120 ሚሊዮን ሰው የሚኖር ቢሆንም፤ ደም የሚለግሱ ሰዎች ቁጥር ገና አንድ ሚሊዮን እንኳን አልደረሰም ሲሉ ያስረዳሉ።

አንዳንዴ መርፌ ፈርተው ደም የማይለግሱ ሰዎች አሉ። ‹‹ሰው ጦር ሜዳ ይሄድ የለ እንደ›› የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ ‹‹እኛ ሰላም ወጥተን እንድንገባ አንድ ወታደር ነፍስ እስከመስጠት ከደረሰ በሰላም ሀገር ቁጭ ብለን ደም መለገስ ትልቅ ጉዳይ ሊሆንብን አይገባም›› ይላሉ።

ልባችን ቅን ከሆነ አንድ መርፌ ብቻ ተወግተን ደም አጥቶ ለመሞት የተቃረበን ሰው ማዳን እንደምንችል ማሰብ ይገባናል። አይደለም መርፌ ነፍሴን እሰጥለታለሁ የምንላቸው ሰዎች አሉ። ሌሎችንም እንደዛ ማየት መልካም ነው የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ ሁሉም ሰው በተቻለው አቅም ደም እንዲለግስ ጥሪያቸውን ያስተላልፋሉ።

አንዳንዶች ደግሞ በውፍረት እና በቅጥነት የሚመስላቸው አሉ። ‹‹አጥንት ስትፈልጉ እንመጣለን›› የሚሉ መኖራቸውን ያነሳሉ። እኛ ደግሞ ስጋ አይደለም የምንፈልገው የሚሉት ሲስተር አሰጋሽ፤ የሁሉም ሰው ደም ክቡር በመሆኑ ደም ለመስጠት ለሚመጡ ሁሉ ክብር እንሰጣለን ሲሉ ይናገራሉ።

ወንጀል ሰርተው ቅጣት እንዲቀልላቸው ከዚህ በፊት ደም የለገሱትን ወረቀት ለማጻፍ የሚመጡ እና የትምህርት እድል ወደ ውጭ ሀገራት በሚያገኙበት ወቅት ለማጻፍ የሚመጡ እንዳሉ ያነሳሉ። ደም መስጠት በዚህ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ያስቀምጣሉ።

## ቀጣይ እቅድ

ሲስተር አሰጋሽ ለ117ኛ ጊዜ ደም የለገሱት የዓለም ደም ለጋሾች ቀን በጅማ ከተማ በሚከበርበት ወቅት ሲሆን፤ በቀጣይም እድሜያቸው እስከሚያግዳቸው ድረስ ደም ለመለገስ ዝግጁ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

# ባህልና ቱሪዝም



# ጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት- የገበታ ለሀገር ሌላኛው ገፀ በረከት

**ዳግም ከበደ**

የገበታ ለሀገር ፕሮጀክት አካል የሆነው የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ጨምሮ በርካታ ባለስልጣናት በተገኙበት በይፋ ተመርቋል። ፕሮጀክቱ በቱሪዝም መዳረሻ ልማት ሥራዎች እየተመዘገቡ ካሉ ውጤታማ ሥራዎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳል።

የቱሪዝምና ሆስፒታሊቲ ዘርፉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለይ በመዳረሻ ልማት ዙሪያ ከፍተኛ እድገት እያስመዘገበ መሆኑን እየተመለከትን ነው። ይህ ብቻም ሳይሆን የተፈጥሮ መስህቦችን መሰረት ያደረጉ አዳዲስ መዳረሻዎችን (ወንጪ፣ ሀላላ ኬላ፣ የጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅ ጨምሮ) ከማስተዋወቅ አንፃር ስኬታማ ተግባራት መከናወናቸውንም መረጃዎች ያመለክታሉ።

ጎርጎራም የዚሁ አካል ነው። ጎርጎራ ፊትም በቱሪስት መስህብነት ቢታወቅም፣ ይህን እምቅ አቅሙን በመመልከት በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ቱሪስቶችን በእጅጉ ሊስብ በሚያስችል መልኩ ግንባታ ተካሂዶለታል፡፡ እንደታሰበውም የቱሪስት ፍሰቱን በእጅጉ መጨመር እንደሚችል ይጠበቃል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "ገበታ ለሀገር" ውጥን እንደ ሀላላ ኬላ፣ ጨበራ ጩርጩራ፣ ወንጪ እና ጎርጎራ ያሉ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማልማት እና በአካባቢያቸው የሚገኙ ልዩ የተፈጥሮ ሀብቶችን አጉልተው በማሳየት ረገድ ከፍተኛ እመርታን አስመዝግቧል። እነዚህ ጥረቶች ለዘላቂነት እና ለአካባቢ ጥበቃ ቅድሚያ በመስጠት ቱሪዝምን ለማሳደግ፣ ሥራ ለመፍጠር እና በዙሪያው የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ያለሙ ናቸው።

‹‹ቱሪዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማስገኘት እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሥራዎችን በመደገፍ በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል›› የሚለው የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት መልእክት፤ ለጠቅላላ ሀገራዊ ምርት (GDP) በሚያደርገው ቀጥተኛ አስተዋፅኦም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ያመለክታል።

በኢትዮጵያም ቱሪዝም መንግሥት ላስጀመረው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የማዕዘን ድንጋይ ሲሆን፤ ከአምስቱ ቁልፍ ምሰሶዎች አንዱ ነው። እንደ "ገበታ ለሀገር" ያሉ ሥራዎች የቱሪዝም ዘርፉን ለማዳበር፣ ብዙ ጎብኚዎችን ለመሳብ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማነቃቃት፣ የሥራ እድሎችን ለመፍጠር፤ መዳረሻዎችን ለማልማት እና ለማሻሻል ታልመው በሥራ ላይ በመዋል ላይ ይገኛሉ።

ከጽህፈት ቤቱ መልእክት እንደምንረዳው፤ የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ምረቃ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አራት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ መዳረሻዎችን በ "ገበታ ለሀገር" ውጥን ስር ለማልማት ያሳዩት ቁርጠኝነት ተጨማሪ ማሳያ ሲሆን፤ በ2012 ቃል በገቡት መሰረት ገንብተው ተጠናቆ ማስረከባቸውንም ያመላክታል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ራዕያቸው ተስፋፍቶ በግንባታ ላይ ያሉ ሰባት ተጨማሪ መዳረሻዎችን ለማልማት ያቀደ "ገበታ ለትውልድ" የተሰኘ አዲስ ፕሮጀክትም አስጀምረዋል።

የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት በተመረቀበት ወቅት ስለ ፕሮጀክቱ ስኬታማነት የተናገሩት የአማራ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ አረጋ ከበደ፤ የገበታ ለሀገር አካል የሆኑትና በክልሉ እየተገነቡ ያሉት ፕሮጀክቶች ለማህበረሰቡ ፋይዳ ያላቸው ፕሮጀክቶች መሆናቸውን ገልፀዋል። ወሳኝ በሆነ መልኩ የቱሪዝም ፍሰትን የሚጨምሩ፣ ለአካባቢው የልማት ትስስር የስበት ማእከል ሆነው የሚያገለግሉ፣ በትልቁ የሥራ እድል የፈጠሩ ለሕዝቡ የተበረከቱ ታላቅ ገፀ በረከቶች መሆናቸውንም ተናግረዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ፤ የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት በግል ባለሀብቱ ዘንድ ለቱሪዝም ልማት አቅም የሆኑ የኢንቨስትመንት ተግባራትን በማከናወን አካባቢውን ለማልማት የሚያስችል መነሳሳትን ፈጥሯል። ይህ ፕሮጀክት በኮንስትራክሽንና በቱሪዝም ልማት ላይ ለተሰማሩ አልሚዎች በአጠቃላይ በፕሮጀክት አስተዳደር በተለይም ደግሞ በጥራት ሥራ አመራር ረገድ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ ነው። ከዚህም በላይ በጣና ሀይቅ ዳርቻ አካባቢ በምን አይነት የልማት ዘርፎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ፣ተግባራቱንም በምን ያህል የጥራት ደረጃ ማከናወን እንደሚያስፈልግ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ከፍተኛ የሥራ ደረጃ አስቀምጧል። ከሁሉም በላይ የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት የመንግሥትን የሥራ ፈጣሪነት ጠባይና ፍላጎት በግልፅ ያመላከተ ነው።

አቶ በቀለ ኡማ የቱሪዝም ባለሙያ ናቸው። በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል መምህር፣ አማካሪ፣ ተመራማሪ እንዲሁም የአስጎብኚ ድርጅት ባለቤትነት ሆነው በዘርፉ ለዓመታት ሰርተዋል። የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች አካል የሆነው የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት መመረቅን አስመልክቶ ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ባደረጉት ቆይታ እንዳሉት፤ ጎርጎራንና አካባቢውን በአስጎብኚነት በሚሰሩበት ወቅት የመመልከት አጋጣሚው ነበራቸው። ይህ ስፍራ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት ውስጥ ከታቀፉት መካከል በመሆኑና በኢኮ ሪዞርትነት ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የመዳረሻ ልማት ተሰርቶለት በመመረቁ ተደስተዋል።

በአጠቃላይ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በፕሮጀክቱ (በገበታ ለሀገር) ታቅፈው የተሰሩትና እየተሰሩ የሚገኙት ሁሉ አበረታች ውጤት የታየባቸው መሆናቸውን አቶ በቀለ ይናገራሉ። ‹‹በመንግሥት ደረጃ ታቅደው እየተሰሩ ያሉ ትላልቅ የመዳረሻ ልማቶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አላቸው›› የሚሉት የቱሪዝም ባለሙያውና መምህሩ፤ በግል ባለሀብቱ አቅም የማይሰሩ የመብራት፣ ውሃና ሌሎች መሰረተ ልማትን ጨምሮ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሬ የሚጠይቁ ግንባታዎች በመንግሥት መከናወናቸው አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ። ይህም ዘርፉ የሚፈለገውን እድገት እንዲያመጣ መሰረት የሚጥል መሆኑን ያስረዳሉ።

የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርትም በመንግሥት አቅም ከተሠሩ ፕሮጀክቶች መሀል አንዱ እንደሆነ ጠቅሰው፣ በመስህብ ቦታው ላይ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ቱር ኦፕሬተሮች ጎብኚዎች እንዲመለከቱት የሚወስዱበት ተመራጭ መስህብ መሆኑን አስታውሰዋል። ይሁን እንጂ ከዚህ ቀደም የቱሪስት አገልግሎት ሰጪዎች በጥራትና በሚፈለገው ደረጃ የተሟሉ እንዳልነበሩ አንስተው፤ የጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝም መገንባቱ ይህንን በላቀ ጥራት የሚያረጋግጥ እንደሆነ ይናገራሉ።

‹‹የጎርጎራ ፕሮጀክት ተግባራዊ መሆን በዋናነት ለክልሉም ሆነ በአካባቢው ለሚኖር ማህበረሰብ ጠቀሜታ አለው›› የሚሉት አቶ በቀለ፤ በተለይ ማህበረሰቡን ያቀፈ የኢኮ-ቱሪዝም እንቅስቃሴ እንዲኖር በማሰብ ግንባታው መከናወኑ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች እንደሚኖሩት ይጠቁማሉ። ከዚህ ውስጥ የሥራ እድል ፈጠራ፣ የመሰረተ ልማት ተጠቃሚ (የመብራት፣ ውሃና ሌሎችንም ጨምሮ) የመሆን እድል ይዞ እንደሚመጣ ጠቅሰዋል።

አንድ መዳረሻ ሲለማ ማህበረሰቡ በጋራ እንዲያድግ በር ይከፍታል የሚሉት አቶ በቀለ ኡማ፤ የቱሪዝም መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳብም ማህበረሰቡን በመሰረተ ልማት፣ እንዲሁም በሥራ እድል ፈጠራ (በሪዞርቱ በየእርከኑ የሚቀጠሩ ባለሙያዎችን) ተጠቃሚ ማድረግ መሆኑን ይናገራሉ። የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርትም ይህንን መስፈርት እንደሚያሟላ ነው ያመለከቱት። በተለይ ሙሉ ለሙሉ ወደ ሥራ ሲገባ ነዋሪው የምግብ ጥሬ እቃ እንዲያቀርብ፣ ባህላዊ ቁሶችን፣ በራሱ በማህበረሰቡ የተዘጋጁ ባህላዊ ምግቦችን፣ የሚከራዩ ቁሳቁሶችን ጨምሮ ለመዝናኛ ጉዞ የሚያገለግሉ እንደ ፈረስ ያሉ መጓጓዣዎችን በማቅረብ እድል የሚከፍት እንደሆነ ያስረዳሉ።

የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት በሚገኝበት አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች መዳረሻውን እንደራሳቸው እንዲመለከቱት ቀዳሚ ተጠቃሚዎች መሆን ይገባቸዋል የሚሉት የቱሪዝም ባለሙያውና መምህሩ፤ ይህ ተግባራዊ የሚደረግ ከሆነ መዳረሻው ዘላቂ እንዲሆንና የሚፈለገውን አገልግሎት ለጎብኚዎች እንዲሰጥ ተግባራዊነቱ ሊረጋገጥ ይገባል ይላሉ። ይህ አካሄድ ለጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ብቻ ሳይሆን በሀገሪቱ ልዩ ልዩ መስህብ ስፍራዎች እየተሰሩ ባሉ መዳረሻዎች ላይ ተግባራዊ መሆን እንደሚገባውና የፕሮጀክቱ ቀዳሚ ተጠቃሚ የአካባቢው ማህበረሰብ መሆን እንደሚኖርበት ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ፣ በሰው ሰራሽ እንዲሁም በባህል በርካታ የሚጎበኙ ቦታዎች አሏት የሚሉት አቶ በቀለ፤ እነዚህን ሀብቶች የገበያ ስልት በመንደፍ፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ካላቸው ታዋቂ ሰዎች እና ልዩ ልዩ ተቋማት ጋር በመስራት እንደ ሌሎች ጎረቤት ሀገራት (ኬንያ፣ ኡጋንዳ) ተፅእኖ ፈጣሪ በሆኑ መገናኛ ብዙኃን ላይ ማስተዋወቅ እንደሚገባ መክረዋል። በተለይ በቅርቡ ታዋቂ ሰዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማምጣት መጀመሩና የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶችን ጨምሮ ልዩ ልዩ መዳረሻዎችን ማስጎብኘቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ መስህቦቿን እንድታስተዋውቅ እንደሚያግዛት ይናገራሉ። በቅርቡ የተመረቀው የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርትም ከዚህ አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ያስረዳሉ።

ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው የመዳረሻ ልማት ሥራ በጎርጎራና ሌሎች አካባቢዎች መሰራቱ ተገቢ መሆኑን የሚያነሱት አቶ በቀለ ኡማ፣ ይህ ጥረት ይበልጡኑ ስኬታማ እንዲሆን ሌሎች መሰረታዊ ነገሮች መኖራቸውንም ይገልፃሉ። ከእነዚህ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የቱሪዝም ባለሙያዎች መስህቦቹን እንዲመሩት ማድረግና ተገቢውን ባለሙያ በተገቢው ቦታ ማስቀመጥ የሚለው አንደኛው መሆኑን አመልክተዋል።

‹‹ኢኮ ቱሪዝም የማህበረሰቡን ሀብት ለማህበረሰቡ ማዋል ነው›› የሚሉት የቱሪዝም ባለሙያው፣ ይህ እንደ ጎርጎራ ባሉ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ የተሻለ ውጤት ለማምጣትም መንግሥትና የግሉ ዘርፍ በሌሎች መሰል ፕሮጀክቶች ላይ በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል። በተጨማሪም በጎርጎራ ኢኮ ሪዞርትና በሌሎችም ፕሮጀክቶች (በቅርቡ በገበታ ለሀገር የተገነቡ) በግል ባለሀብቶች (በአካባቢው ተወላጆች በማደራጀትም) እንዲተዳደሩና የተሻለ አገልግሎት በዘላቂነት መስጠት እንዲችሉ መመቻቸት ይኖርበታል። መሠረተ ልማቶችን ከመገንባት ባሻገር መንግሥት እነዚህን ፕሮጀክቶች የማስተዳደር ኃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ ማስረከብ ይገባዋል በማለትም ሃሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

### እንደ መውጫ

የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ላለፉት ዓመታት በከፍተኛ ትኩረትና የጥራት ደረጃ ግንባታው ሲከናወን ቆይቶ ሐምሌ 6 ቀን 2016 ዓ.ም ተመርቋል። ከወንጪ ደንዲ ኢኮ ሎጅ፣ ከሀላላ ኬላ እንዲሁም ከጨበራ ጩርጩራ የዝሆን ዳና ሎጅ ቀጥሎ በገበታ ለአገር ፕጀክቶች ውስጥ ተካትተው ግንባታቸው ከተጠናቀቁ መዳረሻዎች ተርታም ተቀላቅሏል።

የቱሪስት መስህብ እንደነበረች የሚነገርላት ጎርጎራ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ሰላም በመጥፋቱ የጎብኚው ቁጥር እየተቀዛቀዘ መምጣቱን መረጃዎች ያመለክታሉ። ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ልዩ ልዩ አካባቢዎች ከሚስተዋለው የሰላም መቀዛቀዝ ሲወጣ የጎርጎራ ኢኮ ሪዞርት ፕሮጀክት ከባህር ዳር እና ጎንደር እንዲሁም በዙሪያው ካሉ የቱሪስት መስህቦች ጋር ተሳስሮ ከፍተኛ የምጣኔ ሀብት ጠቀሜታ ያስገኛል ተብሎ ይጠበቃል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት

ዋለልኝ አየለ

የዓለም ልዕለ ኃያል የሆነችው፣ የዓለም ሀገራትን እኔ ቅኝ ካልገዛኋቸው ስትል የነበረችው ማለት ብቻም ሳይሆን ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ፣ ከእስያ እስከ አፍሪካ በርካታ ሀገራትን ቅኝ የገዛችው፣ በዚህም ምክንያት ቋንቋዋ ዓለም አቀፍ ቋንቋ የሆነው እንግሊዝ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ በተጻፈ ሰነድ መተዳደር የጀመረችው በ13ኛው ክፍለ ዘመን (1215) ነው። ይህም ‹‹ማግና ካርታ›› የሚባለው ሲሆን፤ ታላቁ ስምምነት (ሜጋ ቻርተር) የሚል ትርጉም ይይዛል። ከዚህ ከእንግሊዝ ሰነድ በፊት ሌላ የዓለም ሀገር የገዥዎችን ብዝበዛ የሚገድብ መተዳደሪያ ያላት የለችም።

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ፤ ፍትሐ ነገሥት (የነገሥታት ሕግ) የሚባል ነበር። ነገሥታት የሚመሩበት የሕግ ሰነድ ነው። ማግና ካርታ የሚባለውም ሕጉን ያወጡት የእንግሊዝ ነገሥታት ናቸው። በእርግጥ የፍትሐ ነገሥት ሥረ መሰረቱ የግብጽ ኮፕቲክ ነው። ሆኖም ግን ቃሉንም እሳቤውንም ወደ ኢትዮጵያ በማምጣት ፍትሐ ነገሥት ለሺህ ዘመናት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሲመሩበት ኖረዋል። ዛሬ ላይ ማግና ካርታም ሆነ ፍትሐ ነገሥት ተቀይረው ሌላ ቅርጽ ይዘዋል። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን 93 ዓመታትን ወደኋላ መለስ ብለን የመጀመሪያውን የኢትዮጵያ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት እናስታውሳለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን በአጭር በአጭሩ እናስታውስ።

ከ7 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 10 ቀን 2009 ዓ.ም የኢትዮጵያ የጋዜጠኝነት ሙያ ዘመናዊ መልክ እንዲይዝ ግንባር ቀደም ሚና ከተጫወቱት አንጋፋ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የነበሩት ጋዜጠኛና ደራሲ ነጋሽ ገብረማርያም አረፉ። ነጋሽ ገብረማርያም በኢትዮጵያ የእንግሊዘኛ ዕለታዊ ጋዜጣ የሆነው የ‹‹ዘ ኢትዮጵያን ሄራልድ›› የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ዋና አዘጋጅ ነበሩ።

ከ106 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 11 ቀን 1910 ዓ.ም (በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ጁላይ 18 ቀን 1918) ‹‹ማዲባ›› እየተባሉ የሚጠሩት የጸረ አፓርታይድ አብዮተኛው፣ የደቡብ አፍሪካዊው የነፃነት ታጋይና የደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዚዳንት ኔልሰን ሮሊህላህላ ማንዴላ (ማዲባ) ተወለዱ።

ከ89 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 11 ቀን 1927 ዓ.ም የአንጋፋው የሀገር ፍቅር ትያትር ቤት መሰረት የነበረው ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገር ፍቅር ማኅበር›› ተመሰረተ።

ከ8 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 14 ቀን 2008 ዓ.ም ‹‹የኢትዮጵያ የዘመናዊ ትያትር አባት›› በመባል የሚታወቀው አንጋፋው የጥበብ ሰው፣ አባተ መኩሪያ አረፈ።

በዝርዝር ወደምናየው የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት እንለፍ። በነገራችን ላይ ‹‹ዘመናዊ›› የሚለው እና ‹‹የተጻፈ›› የሚለው አወዛጋቢ ናቸው። የመጀመሪየው የተጻፈ የሚለው አይገልጸውም የሚሉ አሉ፤ ምክንያቱም ፍትሐ ነገሥትም ቢሆን የተጻፈ ነበር። ‹‹ዘመናዊ›› የሚለው ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ከፍትሐ ነገሥት ብዙም የማይሻል እና ሃይማኖታዊ ይዘት ያለበት የንጉሡንና መሳፍንቱን ቤተሰብ የሚያስቀድም ስለሆነ ‹‹ዘመናዊ›› ለማለትም አያስደፍርም፤ ምናልባት በዘመኑ ‹‹ዘመናዊ›› የሚለው ይገልጸው ይሆናል። ያም ሆነ ይህ ‹‹ሕገ መንግሥት›› በሚባል ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀውን ሕገ መንግሥት እናስታውስ።

ኢትዮጵያ እንደ ብዙዎቹ የአውሮፓና ሌሎች ዓለም አገራት በንጉሣዊ ሥርዓት ስትተዳደር የኖረች ሀገር ናት። በእነዚህ ንጉሣዊ ሥርዓቶች ዘመን የነበረው አስተዳደር ብዙውን ዘመን በተጻፈ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት አልነበረም።

ሆኖም ግን ኢትዮጵያ የተጻፈ ዘመናዊ ሕገ መንግሥት የጀመረችውም በዚያው በንጉሣዊ ሥርዓቱ ዘመን ነው። ምንም እንኳን ከሥርዓት ለውጥ በኋላ የሚመጣው መንግሥት ቢቀያይራቸውም የመጀመሪያውን የተጻፈ ሕገ መንግሥት የጀመረችው ግን በንጉሳዊ ሥርዓቱ ዘመን ነው።

በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የህግ ባለሙያ የሆኑት ሚኪያስ በቀለ በአዲስ ማለዳ ጋዜጣ የጻፉትን ጥናታዊ ጽሑፍ፣ የታሪክ ጸሐፊው ፍስሐ ያዜ ‹‹የኢትዮጵያ የአምስት ሺህ ዘመን ታሪክ ቅጽ 2›› መጽሐፍ እና ከልዩ ልዩ ድረ ገጾች ያገኘናቸውን መረጃዎች ዋቢ አድርገን እናስታውሰው።

ንጉሰ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን ዘመናዊ (የተፃፈ) ሕገ መንግሥት ያጸደቁት ከ93 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም ነው። ሕግ መንግሥቱ ሲጸድቅ ንጉሱ የተናገሩትን የፍስሐ ያዜ መጽሐፍ እንዲህ ይነግረናል።

‹‹...ሕግ ለሰው ከሁሉ የበለጠ የሚጠቅም መሆኑን ማንም አይስተውም። መከበርም መጠቀምም የሚገኙት በሕግ መተካከል የተነሳ ነው። መዋረድም መጎዳትም የሚመጡት በሕግ መጓደል የተነሳ ነው። ግፍ እና በደልም የሚበዙት ሕግ ባለመቆሙ ነው....››።

በንጉሣዊ ሥርዓቱ ዘመን በሕይወት የነበሩ አባቶች ሲያወሩ እንደምንሰማው በዘመኑ ‹‹በሕግ አምላክ!›› የሚባል ነገር ነበር። ‹‹በሕግ አምላክ!›› ከተባለ ምንም ዝንፍ አይልም። ወደታች የሚወርድ የወንዝ ውሃ ‹‹በሕግ አምላክ!›› ሲባል ይቆማል ይላሉ አባቶች። አባባሉ ግነት እንዳለው ግልጽ ነው፤ ዳሩ ግን የሕግን ሃያልነት ለመግለጽ የተጠቀሙት ነው። በዚህ እሳቤ ውስጥ ነው የመጀመሪያው ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት የጸደቀው።

የፍስሐ ያዜ መጽሐፍ እንደሚነግረን፤ ሕገ መንግሥቱ ከመጽደቁ በፊት በመሳፍንቱ እና በመኳንንቱ መካከል ከፍተኛ ክርክር ነበር። ጠቅለል ሲደረግ፤ የመሳፍንቱ ሀሳብ ኢትዮጵያ በአውራጃ ተከፋፍላ የመሳፍንቱ የበላይነት እንዲቀጥል ነው። ሥልጣንም ለልጅ ልጆቻቸው እንዲተላለፍ ነው፤ ዳሩ ግን ወንጀል ሰርተው ከተገኙ ከርስታቸው እንዲነቀሉ የሚል ነው።

የመኳንንቱ ሃሳብ ደግሞ፤ በአጭሩ ሹመት በዘር መሆን የለበትም የሚል ነው። ንጉሱም አስታራቂ ሃሳብ ሰጥተው መሳፍንቱንም መኳንንቱንም ያካተተ እንዲሆን ተደረገ። በንጉሰ ነገሥቱ ይሁንታ ማንም ሊሾም እንደሚችል ተነገረ። በዚህ መንገድ ሕገ መንግሥቱ ሲጸድቅ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱና ሚኒስትሮች አብረው ሆነው ነው።

የሕግ ምሁሩ ሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ደግሞ ስለዚሁ ሕገ መንግሥት የሚከተለውን ይነግረናል።

‹‹... ሕገ መንግሥቱ የተረቀቀው በንጉሡ ቀጥተኛ ትዕዛዝ ሲሆን፣ ያረቀቁትም በሩስያ የተማሩ ተክለሐዋርያት ተክለማርያም የሚባሉ ግለሰብ ነበሩ። ደጃዝማች ተክለሐዋሪያት ሕገ መንግሥቱን ለማርቀቅ አጼ ኃይለሥላሴ በቀጥታ ጥያቄ እንዳቀረቡላቸው፣ ውይይታቸውን በማካተት ስለ ግለ ሕይወት ታሪካቸውን በጻፉት መጽሐፍ ላይ አስፍረዋል...››።

ንጉሡ ሕገ መንግሥቱን ለማስረቀቅ እና ለማውጣት ምክንያት የሆናቸው ሀገሪቷ ተራማጅ እና ሥልጡን መሆኗን ለዓለም ለማሳተዋወቅ ነው። የሚኪያስ በቀለ ጥናት ተከታዮቹን መረጃዎችም ይነግረናል።

ደጃአዝማች ተክለሐዋሪያት ሕገ መንግሥቱን ከጃፓኑ (የመጂ ስርወ መንግሥት) ሕገ መንግሥት ላይ በመገልበጥ ቢያረቁትም፤ ከሚኒስትሮች እና የክፍለ ሀገር መኳንንቶች የተውጣጣ 11 አባላት ያሉት የሕገ መንግሥት አርቃቂ ኮሚቴ ተቋቁሞ ነበር። ኮሚቴው የእንግሊዝና የጃፓን ሕገ መንግሥቶች ተተርጉመው ቀርበውለት ተወያይቶበት እንደነበር እና በቀጥታ ወደ ንጉሡ ተልኮ ነው የጸደቀው።

ንጉሡ ሕገ መንግሥቱን ከማጽደቃቸው በፊት ብላቴን ጌታ ሕሩይ እና ራስ ካሳ ከሚባሉ አማካሪዎቻቸው ጋር መክረዋል። ሕዝብ አልተወያየበትም በሚል የሕገ መንግሥቱ ሰነድ ከንጉሡ ለሕዝብ የተሰጠ ሥጦታ ተደርጎም ይቆጠራል።

ይህ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት ንጉሡን ሲያስተች የቆየ ነው። በዚያ ንጉሳዊ ዘመን ቢያንስ የተጻፈ ሕገ መንግሥት ማስጀመራቸው ያስመሰግናቸዋል እንጂ ይዘቱ ግን ለንጉሡ ያደላ ነበር። እነዚህን አንቀጾች እንጠቃቅስ።

አንቀጽ ሁለት፡- የኢትዮጵያ መሬትም፣ ሕዝብም፣ ሕጉም በጠቅላላው የንጉሠ ነገሥት ነው።

አንቀጽ ሦስት፡- የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰለሞን እና ንግሥት ሳባ ከተባለችው ኢትዮጵያዊ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሳህለሥላሴ ዘር ከተወለደው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እንዳይወጣ በሕግ ተወስኗል።

አንቀጽ አምስት፡- ንጉሰ ነገሥቱ የነጋሲ ዘር በመሆኑና ቅብዓ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ፣ ማዕረጉ የማይገሰስ ኃይሉ የማይደፈር ሆኖ በቆየውም ልማድ በአዲሱም ሕግ በሚገባው ሁሉ ይከበራል። ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የተነሳ ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት አንቀጾች ንጉሱን በሕግ ባለሙያዎች እነሆ ዛሬ ድረስ ተወቃሽ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በታሪክ ጸሐፊዎች ግን የዘመኑ እና የሥርዓቱ ባህሪ ነው የሚል ሙግት አለ። ቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ለሺህ ዘመናት የኖረ ንጉሣዊና ልማዳዊ ሥርዓትን ነው አዲስ መንገድ ያስጀመሩት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈ ሕግ እንዲኖረው ያደረጉት... የሚሉ አሉ።

ያም ሆነ ይህ፤ የመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ነው። ለዛሬው የምናስታውሰው የመጀመሪያው የጸደቀበትን ስለሆነ እንጂ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎች አንቀጾች ባስነሱት ቅሬታና ሙግት በ1948 ዓ.ም ሕገ መንግሥቱ ተሻሽሏል።

የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ሕገ መንግሥት ለዘውዳዊ ሥርዓቱ ያደላ ቢሆንም ያመጣቸው ለውጦችም በታሪክ በበጎ ተጽፈውለታል። ለምሳሌ፤ ማንኛውም መሳፍንት እንዳለፈው ዘመን በግሉ ከውጭ ሀገራት ጋር መጻጻፍ አይችልም። መሳሪያ እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በግሉ መቀበል አይችልም። መሳፍንቱን በቁጥጥሩ ሥር ማድረግ ችሏል።

በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፓርላማ የተመሰረተውም በዚሁ በመጀመሪያው የተጻፈ ሕገ መንግሥት ነበር። ይሄው ሐምሌ 9 ቀን 1923 ዓ.ም የጸደቀው የንጉሡ ሕገ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶችን አቋቁሟል። ምክር ቤቶቹም የሕግ መወሰኛ (ላዕላይ) ምክር ቤት እና የሕግ መምሪያ (ታህታይ) ምክር ቤት የሚባሉት ናቸው። በዛሬው ዓውድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደማለት ነው።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት ንጉሡን ለረዥም ጊዜ ካገለገሉ መኳንንት፣ ሚኒስትሮች፣ ዳኞች እና የውትድርና መኮንኖች ውስጥ በቀጥታ በንጉሡ የሚመረጡ ናቸው። አባላቱ የመሳፍንት ዘር ባይሆኑም መንግሥትን ያገለገሉ ከሆነ ከተራ ዜጎችም ይመረጣሉ። ይሄውም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 31 ላይ ተቀምጧል።

የሕግ መምሪያው ምክር ቤት አባላት ደግሞ ‹‹ሕዝቡ የራሱን እንደራሴ መምረጥ እስከሚችል ድረስ›› በሚል በመኳንንቱ እና በሹመኞች ተመርጠው እንደሚላኩ ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 32 ይደነግጋል።

አንድ አባል በተመሳሳይ ጊዜ የሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን አይችልም። ምክር ቤቶቹ አራት ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣልያን ወረራ ጊዜ ሥራቸውን አቁመው ቆይተው በድጋሚ ሥራቸውን የጀመሩት በ1933 ዓ.ም መሆኑን አቶ ቃልዓብ ታደሰ ስለ ሕገ መንግሥት ታሪክ በጻፉት መጽሐፍ ላይ አስፍረዋል።

ረቂቅ ሕጎች ከተለያዩ ሚኒስትሮች የሚቀርቡ ሲሆኑ የመጨረሻው ሕግ የማውጣት ሥልጣን ግን የንጉሡ ነበር። ረቂቅ ሕጎች ግን በሁለቱም ምክር ቤቶች ውይይት ይደረግባቸዋል። የትኛውም ምክር ቤት በሚመጡ ረቂቅ ሕጎች ላይ ሃሳብ ካለው በፕሬዚዳንቱ (አፈ ጉባኤ) አማካኝነት ለንጉሡ ያቀርባል። በሁለቱ ምክር ቤቶች መካከል በረቂቅ ሕጎች ላይ አለመግባባት ካለም የሚፈታው በንጉሡ የመጨረሻ ቃል ነው።

በነገራችን ላይ የንጉሡ ሕገ መንግሥት በ1948 ዓ.ም ሲሻሻል የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በሕዝብ የሚመረጡ እንዲሆን ደንግጓል። የሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባላት በመኳንንትና ሹመኞች መመረጣቸው ቀርቶ በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ ሲደረግ፤ በሕዝብ የሚረጡት የሕግ መምሪያ ምክር ቤቱ አባላት ከ25 ዓመት በላይ መሆን፤ የራሳቸው ርስት ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲኖራቸው ይገባል። የሥራ ዘመናቸውም ለአራት ዓመታት ነው። ይህንንም ተከትሎ በሀገሪቷ የመጀመሪያው ምርጫ በ1949 ዓ.ም ተደርጓል።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤቱ አባላት ግን አሁንም በንጉሡ ነው የሚመረጡት፤ የሚያገለግሉትም ለስድስት ዓመታት ያህል ነው።

ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ 17 ኢትዮጵያውያን እና 13 የውጭ ዜጎችን ያካተተ የሕጎችን ጥራዝ የሚያዘጋጅ ኮሚቴ አቋቋሙ። ኮሚቴው የሚሰበሰበው እና ሥራውን ይሰራ የነበረው በጊዜው ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በአሁኑ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ትምህርት ቤት ውስጥ ነበር።

ከተረቀቁት የሕግ ጥራዞች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል።

የ1952 ዓ.ም ፍትሐ ብሔር፣ የ1958 ዓ.ም የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት፣ የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ፣ የ1954 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት፣ የ1952 ዓ.ም የንግድ፣ እና የ1952 ዓ.ም የባህር ሕጎች ናቸው። ሕጎቹ የጸደቁትም ከ1949 ዓ.ም እስከ 1958 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ነበር።

በዚያን ጊዜ ከተረቀቁት ስድስት ሕግጋት አምስቱ የተለያዩ ማሻሻዎች እየተደረገላቸው እስከ ዛሬ ተፈጻሚ ሲሆኑ አንዱ (የወንጀለኛ መቅጫ) ሕግ ግን በ1997 ዓ.ም በሌላ እንደተተካ የሕግ ምሁሩ ሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ያመለክታል።

የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት ከላይ የጠቃቀስናቸውን ይመስላል። ለመሆኑ ከዚህ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት በፊት የነበረው ምን ነበር የሚለውን ከሕግ ምሁሩ ሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ጥቂቱን እናካፍላችሁ።

ማህበረሰቡ ለዘመናት ሲተዳደር የቆየው ከአስተዋይ (አመዛዛኝ ሰው/ዳኛ) ውሳኔ በሚመነጭ ሕገ ልቦና፣ ከአይሁድ፣ ክርስትና እና እስልምና ሃይማኖቶች የሚመነጩ ሕገ ሃይማኖት፣ በሕጎች ዙሪያ ከሚሰጡ የሊቃውንት ትምህርት፣ በስምምነት ከሚገኙ እና በተስማሚዎቹ ላይ ብቻ ከሚፈጸሙ ልማዳዊ ወጎች፣ አንድ ዓይነት አሠራር ለረዥም ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋሉ ምክንያት በተለዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ በስምምነት የሚፈጸሙ ልማዳዊ ሕግጋት፣ እና የአፈ ንጉሥ ችሎት ፍርዶች ናቸው።

ኢትዮጵያን ከ1426 ዓ.ም እስከ 1460 ዓ.ም ያስተዳደሩት አጼ ዘርዐ ያዕቆብ የተጠረዘ እና ወጥ ሕግ ለሀገሪቱ እንዳበረከቱም የሚኪያስ በቀለ ጥናታዊ ጽሑፍ ያሳያል። አጼ ዘርዐ ያዕቆብ በመጀመሪያ ‹‹ፈውስ መንፈሳዊ›› የሚባል በይዘቱ ሃይማኖታዊ የሆነ ባለ 68 አንቀጽ የሕግ ሰነድ በቤተ ክህነት ምሁራን እንዳስረቀቁ እና ለአጭር ጊዜ ሀገሪቷን እንዳስተዳደሩበት ይገልጻሉ።

ቀጥሎም ሀገሪቷን ለዘመናት ሲያስተዳድር የቆየው ‹‹ፍትሐ ነገሥት›› የሚባል በይዘቱ ሃይማኖታዊና ምድራዊ ሕግጋትን ያካተተ የሕግ ሰነድ ለአገሪቷ ያስተዋወቁት አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ናቸው። ፍትሐ ነገሥት ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን የሚያስተዳድር 22 አንቀጽ እና 801 ንዑስ አንቀጾች፤ ምድራዊ (ዓለማዊ) ኩነቶችን የሚገዙ ደግሞ 29 አንቀጾች እና 1033 ንዑስ አንቀጾችን ያካተተ ነው።

በእነዚህ ልማዳዊ፣ ሃይማኖታዊና ሕገ ልቦናዊ ሕጎች ሲተዳደር የኖረው የኢትዮጵያ የነገሥታት ሥርዓት በ1923 ዓ.ም በቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመናዊ የተጻፈ ሕገ መንግሥት አጸደቀ የሚለው ግን እነሆ በታሪክ ተቀምጧል።

# የዝነኞች ገጽ

# የፈገግታ እናት



ሙሉጌታ ብርሃኑ

ፈገግታ... የህይወት ምንጭ ጠብታ...የሰው ልጆች ሁሉ ውስጣዊ ልምላሜ ነው። የጥርስን ነጸብራቅ ፊት ላይ ያስቀምጣል። ደስታን እያፈካ ሀዘንን ያከስማል። ከስጦታዎችም ሁሉ ትልቁ ስጦታ ይኼን ለመስጠትና ለመቀበል መታደል ነው። እንዲህ አይነት ሰዎችም ከማንም በላይ ለልባችን ቅርብ ሆነው ይታያሉ። እነርሱ ተጨንቀው ወልደው ፈገግታን ለኛ ይሰጡናል። ባኮረፈች ዓለም ውስጥ ፈገግታና ሳቅን መፍጠር እጅግ ፈታኙ ቅጽበት ነው። እናም መመረጥን ይሻል።

በእያንዳንዱ ድራማዊ መድረኮች ላይ ትወናን እንመለከታለን። ተውኖ ለማስለቀስ ምናልባትም የተዋጣለት አስመሳይ መሆንና ማስመሰል በቂ ሊሆን ይችላል። በትወና ውስጥ አስመስሎ ብቻ ማሳቅ ግን አይቻልም።ለዚህምነውበዓለማችንላይከተመለከትናቸው እልፍ ተዋንያን መሀከል ጥቂቱ ብቻ ሳቅን መፍጠር የሚችሉ ኮሜዲያን ሆነው የምናያቸው። እነርሱ ማለት በደስታና በሳቅ የሚያቀጣጥሉን የህይወታችን ማጣፈጫ ቅመሞች ናቸውና በተመለከትናቸው ቁጥር የፈገግታ ሱስ ያሲዙናል። ውስጣዊ ስሜታችን ከቀልዶቻቸው ጫፍ ጋር ስለሚተሳሰርም እድሜ ዘመናችንን ሁሉ እንድናስታውሳቸው የሚያደርግ ተፈጥሯዊ መስተጋብር መሀከላችን ይፈጠራል። ታዲያ በዚህ ሁሉ መሀከል፣ ለዚህ ሁሉ ነገር እናት ለመሆን መቻል ማለት እንዴትስ ያለው መታደልና መመረጥ ቢኖረው ነው?

በአንድ ማኅበረሰብ ቤተሰብ ውስጥ እናትነት ለአንዲት ሴት ብቻ የሚሰጥ ጸጋ እንደመሆኑ በሀገራችን የኮሜዲ መድረክ ላይ እናትነቱን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተቀበለች እንቁም ታይታለች። “የኮሜዲ እናት!” ተብሎ ከተጠራ ይህች እናት ማን እንደሆነች ለማወቅ ማሰብ አይጠበቅም። አሻሚነት ኖሮትም አያከራክርም። ምክንያቱም ብቸኛዋ ሴት ሆና በብዙ የወንዶች ስብስብ ውስጥ ድንገት ብቅ በማለት የእናትነቱን ማዕረግ የወሰደች፤ ከእንግዳዘር ነጋ ሌላ ሴት የለችምና።

በእንቁ ባለ ጥበብ የአልማዝ ፈርጥ አጊጣና አምራ ድንገት መሀል ላይ የተገኘች አዲስና ክብርት እንግዳ ነበረች። የአንደኛው ዘመን የሳቅ እናትና የፈገግታ ቀዳማዊት እመቤት ነበረች። እናም ታዲያ አንድም በድንቅ ችሎታዋ ሁለትም በቀዳማይነቷ “የኮሜዲ እናት” የሚል ስያሜን ለማግኘት በቃች። ምን ሠርታ ታወቀች? ከተባለ እርሷ ያልሠራችው የለምና...

እንግዳ ዘር የፈገግታ ጥኡም ፍሬ...ቀድማ የበቀለች፣ ቀድማም የደረሰች የኮሜዲው እናት፣ የሳቅ ደምስር ነበረች። ብዙ ሰዎች እርሷን ለመመልከት ሲሉ ተጋፍተው መድረክ ታድመዋል። ብዙ ሰዎችም የራዲዮናቸውን አንቴና እያዞሩ ከፍተው ድምጿን ለመስማት ተቻኩለዋል። ዛሬ እንግዳዘር ነጋ የምትተውንበት ድራማ ይታያል በማለት ተሰባስበው ከቴሌቪዥኖቻቸው መስኮት ፊት ተኮልኩለው ጠብቀዋል። ምክንያቱም እሷ ፈጠራን ትችልበታለች። እየፈጠረችም በቀልዶቿ ሙሉ አዳራሹን ያለ እረፍት ታንከተክተዋለች። በመድረክ፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስትተውን ደግሞ ቢያዩዋትም ሆነ ቢሰሟት ስሜት ባክኖ ከመሬት ጠብ አይልም። በዚህም በዚያም ቀልብን ሰውራ ታፈዛለች። በእነዚሁ ዘርፈ ብዙ ድንቅ ችሎታዋ ምትሀተኛም ጭምር ናት። ከዚያው ላይ ደግሞ የሕዝብን መውደድ ደርቦላት፤ በሕዝብ ፊት እንደ ንጉስ ጌጥ አብረቅርቃ ታይታለች። ይህች ታላቅ የጥበብ ሰው እንደዚህም ሆና በአንደኛው የኋላ ዘመን ታሪክ ውስጥ ነበረች። አንጋፋዋ አርቲስት እንግዳዘር ነጋ...

የሰው ልጅ ሁሉ የራሱ ብቻ የሆኑ በርካታ የህይወት ምዕራፎች ይኖሩታል። እንደማንነቱ ሁሉ በብዙ ክፍሎች የታጨቁ ብዙ ገጾችንም ይደጉሳል። እንደቻለው ሁሉም ህይወቱን ይጽፋታል። እንደጻፈውም ይነበብለታል። በመነሻው ጀምሮም በመጨረሻው ያሳርጋል። የኢትዮጵያን የኮሜዲ መድረክ ስንገልጥ ከፊት እንግዳዘር ነጋን እናገኛለን። በእንግዳዘር ውስጥም እኚህኑ ባለምዕራፍ ገጾችን እንመለከታለን። ምናልባትም ደግሞ የድጓሱ መጀመሪያና መጨረሻ “ገድለ እንግዳዘር” የሚል አርዕስትም እናገኝ ይሆናል። የመጀመሪያው ምዕራፍ በመጀመሪያውም ገጽ ላይ እንግዳዘር ነጋ በ1944ዓ.ም በደብረማርቆስ ከተማ ውስጥ ተወለደች ብሎ ይጀምራል። ሰሜናዊቷ የጓጃም ምድር፣ የደብረማርቆስ የፍቅር አየር ከወዲያው ጠራት። በዚያም ተወልዳ የመጀመሪያውን ምዕራፍ አንድ ገለጠች። የብቃቷ እንቡጥ ፍሬ ያሸተበት የመጀመሪያው ገጽ ልጅነቷ ነበር።

ስለ ጥበብ ተጋድሎዋ የሚጀምረው ወጣት መስላ በታየችበት ወቅት ሳይሆን ገና ታዳጊ ሆና በኖረችባቸው ዓመታት ውስጥ ነበር። በጊዜው ልጅነቷን የተመለከቱ ሁሉ ውበቷ የጥበብ ጽራር እንደነበረ ያውቃሉ። ፊቷ ላይ ካሉት አፍንጫና ዓይኖቿ ይልቅ አንዳች የጥበብ ዓይነስብ እንደተቀመጠባት ይታይ ነበር። ልጅነቷ ላይ ብዙ የጥበብ ገጾች ስለመኖራቸው በርካቶች ያወሱታል። በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በአስኳላ የቀለም ትምህርት ቤቶች ተገኘች። የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ያጠናቀቀችውም በተወለደችበት የደብረማርቆስ ከተማ ውስጥ ነበር። በቀጣይም የትውልድ ቀዬዋን ለቃ ወደ ደብረ ብርሃን ከተማ አመራች። ወደ መምህራን ኮሌጅ በመግባትም በጥሳ ወጣች።

ሁለተኛው የህይወት ምዕራፏም የሚጀምረው ከዚሁ ቀጥሎ ነበር። የኑሮ እንጀራዋም በተማረችበት የመምህርነት ሙያ ላይ አረፈ። ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በመዘዋወር በመምህርነት ስታገለግል ድፍን 11 ዓመታት ተቆጠሩ። በኋላም በኢንፎርሜሽን ሚኒስቴር ውስጥ ተቀጥራ መሥራት ጀመረች። ለተወሰኑ ጊዜያት ስታገለግል ከሰነበተች በኋላም ወደ ሦስተኛው ምዕራፍ ከመሸጋገሪያ መንገዷ ጋር ተገናኘች። በ1979ዓ.ም ወሳኙን የህይወት ምዕራፍ የከፈተችበት ቁልፍ ነበር። እንግዳዘር ነጋ በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ውስጥ የመሥራት ዕድሉን አገኘች፡፡

ከልጅነቷ አንስቶ በውስጧ የተሸከመችው ጥበብ በውስጧ ቢኖርም እንዲሁ በአጋጣሚዎች ካልሆነ በስተቀር ራሷን ለማሳየት የሚሆን አጋጣሚ አላገኘችም። እናም አሁን በትክክለኛው ጊዜና ቦታ መገኛት ካለባት ቦታ የተገኘችው ገና አሁን ነበር። እዚህ ስፍራ ላይ ያላትን ለማውጣት አመቺ ከመሆኑም ውስጧን ለመረዳት ቅርብ የሆኑ ሰዎችንም ጭምር ለመገናኘት ቻለች። በወቅቱም አለባቸው ተካ፣ አስረስ በቀለ እና ልመንህ በተቋሙ ውስጥና በመላው ሀገሪቱ በዋናነትም በኮሜዲው ተወዳጅነትን ያተረፉበት ነበር። ከእነዚህም ጋር አብሮ ወደመሥራት የሚያስገባው ግዙፍ በር ተከፈተላት። የመጀመሪያዋ ሴት ኮሜዲያን ሆናም በቴሌቪዥንና በራዲዮ ብቅ አለች። ብዙዎችም ያላትንና ያመጣችውን አዲስ ነገር ወደዱላት። አደነቁላት። በጥቂት ጊዜያት ውስጥም የዝና ማማው ላይ ወጣች። በዚያን ጊዜ ሴቷ ኮሜዲያን ከተባለ እሷም እንግዳዘር ነጋ ነበረች። እዚህ ቤት ውስጥም የክብር ዘውዷን እንደደፋች ለ20 ዓመታት ያህል ዘለቃለች፡፡

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የነበረው የእሁድ መዝናኛ ዝግጅት ለአፍታም ቢሆን እንግዳዘርን አይዘነጋም። በዚያም ሰሞን ላይ ጀማሪ ሆነው በጥበብ ጉዞ ከጀመሩትና በአሁኑ ሰዓት ከአንጋፋዎቹ ተርታ ከተሰለፉት መሀከል አንዱ ሰይፉ ፋንታሁን ነበር። በወቅቱ የሙያ ትምህርት ቤቱ ከሆኑት አንዷ ናት። በተለያዩ ጭውውትና ድራማዎችም አብረው ለመሥራት ችለዋል። እርሷ የራሷ ብቻም ሳትሆን በነበረችባቸው ጊዜያት አብረው ለሠሩ ሁሉ ደማቅ ጮራ ነበረች። ኮሜዲውን የተሸከሙት ድራማና ጭውውቶች እንደ አደይ አበባ የፈኩበት ጊዜ ነበር። እንግዳዘር ነጋ፣ ከበበው ገዳ፣ አለባቸው ተካ፣ ደረጀ ኃይሌ፣ ሀብሬ ምትኩ፣ ተስፋዬ ካሳ፣ አለልኝ መኳንንት፣ አበበ በለውና አስረስ እንዲሁም ሌሎች ዘመን አይሽሬ በዘመንም አይተኬ ጥምረትና ውህደት ነበሩ።

በበዓላትና በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ላይ የሚያቀርቧቸው ጭውውቶች በሳቅ ነብስን የሚዘሩም ነበሩ። ታዳሚው ከየመቀመጫው እየተነሳ ሁሉ ሆዱን ይዞ ያነፍራል። የእንግዳዘርና የአስረስ በቀለ ጥምረት ደግሞ የተለየ ነበር። በአንደኛው መድረክ እንግዳዘር ለወራት ወንድሟ ጋር ከአሜሪካ ደርሳ የተመለሰችውን የንግስትን ገጸ ባህሪ ትጫወታለች። አስረስ በቀለ ደግሞ ባላገር ዘመዷ ሸዋንግዛውን ነበር። ከጨዋታቸው መሀልም ሸዋንግዛው ስለአሜሪካው ወንድሟ ስለ ጴጥሮስ ይጠይቃታል።

...

“ጴ...ጥ...ሮስ! ትላለህ...በእነርሱ ፒተር ነው የሚባለው። አሁን ለምሳሌ ሙሉ ጎጃምን ታውቃታለህ?”

“አዎ!”

“እሷን አሁን ኤም ጂ ነው የሚሏት። ...ደግሞ ያ ማነው...ዮሐንስን ታውቀዋለህ? እሱም ጆኒ ነው የሚባለው፡፡” ትለዋለች።

“ቆይ ይህቺ አማሪካን ስም ስትገለባብጥ ነው እንዴ የምትኖረው! ..አሁን እንግዲ ጉድ ላመጣልሽ ነው። እኔ አሁን ስሜ ሸዋንግዛው ነው ታዲያ እስቲ አማሪካን እኔን አሁን ማን ብላ ነው የምትጠራው?”

“ማ አንተን?”

“አዎ”

ጥቂት አሰብ አደረገችና “አንተን...አንተንማ ማን መሰለህ... ሸዋ ፊንገር ነው የምትልህ! ...”

...

በሌላ የጥያቄና መልስ ጭውውታቸው ደግሞ ከአሜሪካን የተመለሱ ባልና ሚስት ሆነው ይተውናሉ። በአንድ መድረክ ላይም እንግዳ በመሆን ሁለቱም ከመድረክ ላይ ይወጣሉ። ጠያቂውም “አሜሪካን እንዴት አገኛችኋት?” በማለት ሲጠይቅ፡፡

“አሜሪካንን እኛ አይደለንም ያገኘናት። ማነው ይኼ... ኮሎምበስ ነው ያገኛት፡፡”

“እንግሊዝኛ ይችላሉ?”

...

“አፍኮረስ....ያ!...ኢቨን...የስ..” አንድ በአንድ የሚያውቋቸውን ቃላት ያንጠባጥቡታል።

ከኢትዮጵያ ሰማይ ስር እልፍ የሴት ጠቢባን ወጥተው እጃችንን ከአፋችን ላይ አስደርበውናል። ዛሬ እንዳሉ ሁሉ ትናንትም ነበሩ። በአንደኛው ነገር ላይ ግን የመጀመሪያዋ ሴት ለመባል የቻሉ ጥቂት ናቸው። ከእነርሱም አንዷ እንግዳዘር ነጋ ናት። በሀገራችን የኮሜዲ መድረክ ላይ የትኛዎቹም ሴቶች ሳይወጡበት በፊት ቀድማ ታይታበታለች። “የመጀመሪያዋ ሴት ኮሜዲያን” የሚለውንም ቀዳማይ የክብር አርማ ተቀበለች። በነበራት የ20 ዓመታት ቆይታዋ የሠራቻቸው ሥራዎች ዛሬም ድረስ ከብዙዎች የተለየች እንድትሆን አድርጓታል።

በጭውውትና በድራማው ውስጥ በእርሷ ልክ ወርቃማ ዘመናትን የተቀዳጀ ያለ አይመስልም። አብዛኛዎቹን ድራማና ጭውውቶችን ጽፋ የምታዘጋጀው እራሷ እንግዳዘር ነበረች። የትወና ብቃቷና አድማጭ ተመልካቹን የማዝናናት ልዩ ተሰጥኦዋ ደግሞ ጥርስ የማያስከድን ነበር። ብዙዎች “የኮሜዲ እናት” ብለው እንዲጠሯት ያስገደዳቸውም ይኼው ነበር። ዳሩ እንዲህ ይሁን እንጂ፤ የእርሷ ነገር ግን “ጅብ ካለፈ ውሻ ጮኸ” ዓይነት ነው፡፡

የእንግዳዘርን የችሎታዋን ልክና የውለታዋን ቁና የተረዱ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስለእርሷ ከማውራት አይቦዝኑም። በተለይ ደግሞ የሥራ ባልደረባዋ የነበሩት ከማንም በላይ ያውቋታል። ከእነዚህም አንዱ አስረስ በቀለ ነው። አልሆንልህ እያለው ጊዜን ሲጠባበቅ ቢቆይም ለረዥም ጊዜያት ስለ እንግዳዘር ነጋ አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት ሲያስብ ቆይቷል። እርሷን ለመዘከር የሚሆን አንድ የጥበብ ምሽት የማዘጋጀት ትልቅ ፍላጎት እንዳለው በአጋጣሚዎች ለብዙ ወዳጆቹ አጫውቶም ነበር።

አንደኛው ምዕራፍ ተዘግቶ ሌላም ይገለጣል። ከአንደኛው የህይወት ገጽ ወደሌላኛው እየተሸጋገሩ በሄዱ ቁጥርም ወደ አንድ ነገር እየቀረቡ መሆኑ ግልጽ ነው። አርቲስቷ እንግዳዘር ነጋ የምዕራፍ ሦስት ጀንበሯ ጠልቆ ከአራተኛውና ከመጨረሻው የህይወት ምዕራፍ ላይ ተገለጠች። ሁሉንም የሰው ልጆች አንድ የሚያደርገውም ምናልባትም ይኼኛው ምዕራፍ ነው። በምዕራፍ አንድ የመጣ ሁሉ የመጨረሻውን የምድር ቆይታውን አጠናቆ በምዕራፍ አራት ተመልሶ መሄዱ ግድ ነው። “አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ” የሚለውን የፈጣሪን ቃልና የተፈጥሮን ህግ ጥሶ ለማምለጥ የሚቻለው አንድም የሰው ልጅ የለምና።

በስንብቱም ስጋና አጥንቱን ለመጣበት አፈር መልሶ ይሰጣል። ነብሱንም ለሰጠው ፈጣሪው ያስረክባል። ታላቁን ስምና ሥራውን ግን ለሰው ልጆች በስጦታ ያበረክትለታል። ከአፈሩ ከፍ ብሎ ከመቃብር በላይ የሚታየውም በዚሁ ስጦታው ነው። በህይወት ሳሉ ለመስጠት ያልታደሉም ከሞት ወዲያ ከአንዲት የድንጋይ ሐውልት በስተቀር ሌላ ምንም አይኖራቸውም። ለሰጡቱ ደግሞ ከሞት ወዲያም ህይወት አለ። ሠርተው ያለፉት ሥራ ሁሉ በሚመጣው ትውልድ አደባባይ ላይ የሚቆም የጀግንነትና የመታሰቢያ ሐውልት ሆኖ ይታይላቸዋል። ይህን ለማድረግ የሚችሉ ግን ከብዙ መሀከል ጥቂቶች ብቻ ናቸው። ከእነርሱም እንደ እንግዳዘር ነጋ ያሉቱ ብቻ ናቸው። አርቲስት እንግዳዘር ነጋም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አራተኛውን ምዕራፏ በአውሮፓውያኑ 2004ዓ.ም በድንገት ተዘጋ። ታላላቆች ግን መጀመሪያ እንጂ የሚያልቅ መጨረሻ የላቸውም።

ተገልጦና ተነቦ ከሚያልቀው አራተኛው ምዕራፍ በኋላ ለዘለዓለም በቃላት የማይገለጽ፣ ህልቁ መሳፍርት ገጾች የታጨቁበትና ከምድር እስከሰማይ የሚረዝመው አምስተኛው ምዕራፍ ይቀጥላል፤ ግን ደግሞ አያቆምም። ከዚህ ምዕራፍ ላይ የሚደርሱ አሁንም እንደ እንግዳዘር ያሉት ብቻ ናቸው።

የባለውለታዋ ውለታ ለማስታወስ ምናልባትም የተደረጉ አንዳንድ መልካም ነገሮች ተቀምጠዋል። ስምን ከሰማይ በታች ካለ የምድር ጥላ ላይ ከማሳረፍ በላይ ምን አለና? እንግዳዘር ነጋ ዛሬ ላይ ከአንድ ባንክ ደጃፍ ላይ ግዙፍ ሥራዋ ከስሟ ጋር አቁሞላታል። የኮሜዲው እናት ናትና፤ እናት ባንክም በአዲስ አበባ ተክለሃይማኖት ሰፈር ውስጥ ያለውን ቅርንጫፉን በስሟ ሰይሞታል።

አርቲስት እንግዳዘር ቅርንጫፍ...የእርሷ የጥበብ ህይወትና የአምስተኛው ምዕራፏ ግንድም ከአፈር በላይ ሆኖ በስር ላይ ሌላ ስር እያበቀለ ቅርንጫፎቿን እንደ ሰማይ ከዋክብት፣ እንደ ምድር አሸዋም እያበዛው ይሄዳል። እንደ ወንዝ ዳር ቄጤማ፣ እንደ ጸደይ አበባም ያለመልመዋል። የፈገግታ እናትነቷም በአምስተኛው ሌላ ምዕራፍ በእልፍ ገጾች ሲገለጥ ይሄዳል።

# ዓለም አቀፍ

# የዛምቢያ ፀረ ሙስና ባለሥልጣናት በሙስና ተጠርጥረው ከኃላፊነታቸው ተባረሩ

ሙስናን እንዲከላከሉ የተሾሙት የዛምቢያ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የቦርድ አባላት ራሳቸው ሙስና ውስጥ ተዘፍቀዋል በሚል በሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ከኃላፊነታቸው ተባረሩ። የመንግሥታዊው የፀረ ሙስና ተቋም የቦርድ አባላት ቢያስተባብሉም የሙስና ክስ መቀረቡን ተከትሎ ነው የዛምቢያው ፕሬዚዳንት ሃኪንዴ ሂቺሌማ ለየት ያለ ውሳኔ በማሳለፍ ሁሉንም ከሥልጣን ያሰናበቱት።

የፕሬዚዳንቱ ውሳኔ ይፋ የሆነው የሀገሪቱ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ዋና ኃላፊ ቶማስ ሻማካምባ በፈቃዳቸው ከኃላፊነታቸው መልቀቃቸው ከተነገረ ከቀናት በኋላ ነው። ባለሥልጣኑ በፈቃዳቸው ሥራቸውን ይልቀቁ ወይም በፕሬዚዳንቱ ውሳኔ ከኃላፊነታቸው ይባረሩ በይፋ የታወቀ ነገር የለም።

ከሥልጣን የለቀቁት ኮሚሽነሩ እና የተቋሙ ዋና ዐቃቤ ሕግ ማርሻል ሙቼንዴ ጉቦ በመቀበል የተከሰሱ ሲሆን፤ ሁሉቱም ግን የቀረበባቸውን ክስ ሐሰት ሲሉ አስተባብለዋል።የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ሂቺሌማ ከሦስት ዓመት በፊት ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ የፀረ ሙስና ኮሚሽኑ ባለሥልጣናት በሙስና በተከሰሱ የቀድሞው አስተዳደር ከፍተኛ ባለሥልጣናት ላይ ምርመራ ሲያካሂዱ ቆይተዋል።

አሁን በፀረ ሙስና ኃላፊዎች ላይ የቀረበው ክስም ከዛምቢያ የቀድሞ አስተዳደር ባለሥልጣናት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ነው ተብሏል። በዚህም ምርመራ እየተደረገባቸው ላሉት የቀድሞ ፖለቲከኞች ምርመራቸው ተቋርጦ ምህረት እንዲያገኙ ለማስቻል ገንዘብ ተቀብለዋል ተብሏል።

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ጥቆማ የሰጠው ቀድሞ በፀረ ሙስና ኮሚሽን ውስጥ የቦርድ አባል የነበረው ኦብሪን ካባ የተባለ ግለሰብ እንደሆነ ተገልጿል።ግለሰቡ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ በጽሁፍ ይፋ እንዳደረገው "በወጡ ዘገባዎች መሠረት የፀረ ሙስና ኮሚሽኑ በሙስና ከተዘፈቁ ሰዎች መካከል የተወሰኑት ከፍትህ እና ከተጠያቂነት ነጻ እንዲሆኑ የሚያስችል በሕግ ትርጉም አልባ የሆነ ስምምነት አድርጓል" በማለት ገልጾ ነበር።

ግለሰቡ ጨምሮም በቀደመው የሀገሪቱ አስተዳደር ወቅት የነበረው "ከመከሰስ ነጻ የሚያደርገው ስምምነት" የአሁኑ አስተዳደር "ሙስናን ለመዋጋት ቁርጠኝነት የሌለው በሚያስመስል ሁኔታ" ጥቅም ላይ እየዋለ ነው በሚልም ተችቷል። ኦብሪን ካባ ተበላሽቷል የሚለውን የሀገሪቱን የፀረ ሙስና ኮሚሽንን ለማስተካከል አራት የቦርድ አባላትን ማባረር ብቻ "በቂ አይደለም" በማለት ሙሉ ተቋሙ ለውጥ እንደሚያስፈልገው ጠቁሟል።

የግለሰቡን ክስ ተከትሎ የተቋሙ ዋና ዐቃቤ ሕግ የነበሩት ሙቼንዴ የስም ማጥፋት ክስ መሥርተውበታል። የኮሚሽኑ ሌሎች አባላትም ተመሳሳይ ክስ በኦብሪን ካባ ላይ ሊመሠርቱ ይችላሉ እየተባለ ነው። በፀረ ሙስና ኮሚሽኑ መሪዎች ላይ የቀረበውን ክስ ተከትሎ ከዛምቢያው ፕሬዚዳንት ጽህፈት ቤት በወጣው መግለጫ የተቋሙ የቦርድ አባላት መባረር አስፈለጊ የሆነው "ወሳኝ የሆነውን የፀረ ሙስና ኮሚሽንን ኃላፊነት ለማደስ ነው" ብሏል።

የፀረ ሙስና ኮሚሽኑ ዋና ኃላፊ ቶማስ ሻማካምባ ከሥልጣን መልቀቃቸው ይፋ የተደረገውም ከፕሬዚዳንቱ ጽህፈት ቤት በወጣ መግለጫ ሲሆን፤ ይህም ባለሥልጣኑ በፈቃዳቸው ሥራቸውን ለቀው ሳይሆን ተባረው ነው የሚል ግምትን ፈጥሯል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።



## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ዶፍቶሩ አጎናፍር የተሽከርካሪ ዓይነት ት/ሣይክል የሠሌዳ ቁጥር 1-A18261 ኦሮ የሻንሲ ቁጥር MD6M14PA3N4B00478 የመኪና ሞዴል ትሽስ የሞተር ቁጥር AK4BN4800384 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ/ጠፋብን ብለው በ8/11/2016 አመልክተዋል። የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፣ ከተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ/የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**በቢሾፍቱ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**
**የዱከም ክ/ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም ነስሩ መሀመድ ሰሌዳ ቁጥር 3-71975 ኦሮ ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ኦርጅናል ጠፋብን ብለው በቀን 01/11/2016 አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ ሊብሬ/ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳጃ ትእዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን።

**የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

## አማራ ክልል

በከሳሽ፡- ህዳሴ ቴሌኮም አ.ማ. እና

በተከሰሽ፡- ወ/ሮ ሰሚራ አብደላ ኡመር መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር በተመለከተ ተከሳሽ 25/11/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀነ ቀጠሮ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሚሴ ከጠዋቱ 2፡30 ሰዓት እንድትቀርብ የማትቀርብ ከሆነ ግን ክሱ በሌለችበት የሚታይ መሆኑን የኦሮሞ አሰ/ዞን ከፍ/ፍ/ቤት አዟል።

**በኦሮሞ ብሔ/አስ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**
**የፍታብሔር ዋና የሥራ ሂደት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ አቶ ወርቅነህ ለቺሳ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ትዕግስት ዱጉማ መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ ለ16/11/2016 ዓ.ም 8፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ/ምድብ 8ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል። በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ሱመያ ሰይፉ የመጥፋት ውሳኔ ይሰጥልን ሲሉ አመልክተዋል። ስለሆነም ተጠሪ አቶ ዩኑስ አብዶ ማህዲ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ሐምሌ 19/11/2016ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**
**የካ ምድብ ችሎት**

አመልካች ወ/ሪት ናኒ ሲሳይ ራያ

ተጠሪዎች 1. ወ/ሮ ገነት ሲሳይ ራያ

2. አቶ ዮሃንስ ሲሳይ ራያ
3. ወ/ሮ መድሃኒት ሲሳይ ራያ
4. አቶ ግርማቸው ሲሳይ ራያ
5. ወ/ሪት ኢየሩሳሌም ሲሳይ ራያ

ተጠሪዎች በአድራሻቸው ተፈልገው ሊገኙ ስላልቻሉ ለ23/11/2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ/ምድብ 2ኛ ውርስ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ /አመልካች እነ አቶ ፍሬዘር ነጋሽ እና

በተከሳሽ /ተጠሪ አኪር ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/ግ/ማህበር

መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ምድብ 2ኛ ስ/ክርክር ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ /ተጠሪ በ18/11/16 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በፍርድ ባለመብት አዋሽ ኢንሹራንስ ኩ/አ/ማ እና በፍርድ በለዕዳ አቶ በለጠ ከበደ መካከል ስላለው የፍትሐብሄር ክርክር ጉዳይ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ. ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው እንደ ፍርዱ የማይፈጽሙበትን ምክንያት ቢኖር ይህንኑ ምክንያት በ22/11/2016 ዓ.ም 8፡20 ሰዓት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 2ኛ ባ/ኢ. ችሎት ቀርበው እንዲያስረዱ ታዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ንግድና**
**ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

በከሳሽ እነ አቶ ዘገየ ታመነ ሀብተሚካኤል እና በተከሳሽ ሚ/ር ፔንግ ፋዩን መካከል ባለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በቀን 19/11/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ታዟል። በቀጠሮ ቀን ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ አቶ እንዳለ ደምስ እና በተከሳሽ አቶ አዱኛ ሁነኛው መካከል ስላለው ገንዘብ ለማስከፈል ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ22/11 ቀን 2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ/ከቀኑ 4፡30 ሰዓት የመ/ደ/ፍ/ቤት ለሚ ኩራ ምድብ 5ኛ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት**
**የለሚ ኩራ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ አቶ ፀጋዬ ሽጉጤ እና በተከሳሾች 1ኛ፣ አቶ ያደታ ጣፋ 2ኛ፣ አቶ ተስፋዬ ያደታ

መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተከሳሾች ለ22/11/2016 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ መልሳቸውን በሬጅስትራር በኩል እንዲያያይዙ ክስ ለመሰማት ደግሞ 7/2/2017 8፡30 ሰዓት ላይ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ 10ኛ ፍታብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ማፍ ቢዝነስ ግሩፕ እና

በተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ሞገስ በላይ መረሳ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ምድብ 3ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ23/11/2016 ዓ.ም ከቀኑ 3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ኦሎምፒክ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ፈር ቀዳጁ ኦሊምፒያኖች አሰልጣኝ- ንጉሴ ሮባ

ብርሃን ፈይሳ

ውጤታማው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ የድል ታሪኩ የሚጀምረው በውጪ ሀገር ዜጋ አሰልጣኝ ነው። በስዊድናዊው የኢትዮጵያውያኖች የኦሊምፒክ አሰልጣኝ ኦኔ ኔስካነን የጀመረው ጉዞ በሀገር ውስጥ አሰልጣኞች ተተክቶ በደማቅ ታሪክ መቀጠል ከጀመረም ዘለግ ያሉ ዓመታት ተቆጥረዋል።

በኦሊምፒክ መድረክ ልምድና እውቀትን ቀምረው ለሀገራቸው ስኬት ሲጥሩ ከቆዩ ቀደምት አሰልጣኞች መካከል ደግሞ ግንባር ቀደሙ ንጉሴ ሮባ ናቸው። 25 ዓመታትን ባስቆጠረው የአሰልጣኝነት ህይወታቸውም በርካታ ስመጥር አትሌቶችን በማፍራት የሀገራቸው ባንዲራ እንዲውለበለብ አድርገዋል። ጥቂት ቀናት ብቻ የቀሩትን የ2024 ፓሪስ ኦሊምፒክ ተከትሎም በዛሬው የስፖርት ማህደር አምድ ታላቁን አሰልጣኝ እናስታውሳለን።

በ1933 ዓ.ም ጅግጅጋ የተወለዱት አሰልጣኝ ንጉሴ በሐረር እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተሞች ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። የተፈሪ መኮንን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ንግድ ስራ ኮሌጅን የተቀላቀሉ ሲሆን፤ በዲፕሎማ በመመረቅ በአንድ የግል ኩባንያ ውስጥ ይሰሩ ነበር። በ1949 ዓ.ም ግን የሚሰሩበት ኩባንያ ባለቤት የሆኑት ሰው አዲስ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌዴሬሽን ዋና ፀሐፊ ሆነው መመረጣቸውን ተከትሎ ወጣቱ ንጉሴ በፀሐፊነት እንዲቀጠሩ አደረጉ።

የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሳሉ በአጭር ርቀት፣ እግር ኳስ(የቅዱስ ጊዮርጊስ ክለብ አማካይና አጥቂ ተጫዋች) እና በቦክስ ስፖርቶች ተሳታፊ እንዲሁም ጠንካራ ተፎካካሪ በመሆናቸው በጽህፈት ቤቱ በተቀጠሩበት ዓመት በተለያዩ



ንጉሴ ሮባ ለ37 ዓመት የኢትዮጵያ አትሌትክስ ስፖርትን ከአሰልጣኝነት እስከ አመራርነት አገልግለዋል፤

ውድድሮች ላይ በመሳተፍ እውቅናን ማትረፍ ቻሉ። በወቅቱ በሚደረጉ ውድድሮች የታወቁ አትሌቶችን ጭምር በማሸነፋቸውም ለሜልቦርን ኦሊምፒክ ሊመረጡ ቻሉ። ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈችበት በዚህ ኦሊምፒክ ሀገራቸውን ከወከሉት ብሄራዊ ቡድን አባላት መካከል አንዱ በመሆን በቢሾፍቱ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተው በ100 እና 200 ሜትር ተወዳደሩ። ይሁን እንጂ ዓለም አቀፍ የውድድር ልምድ ስለሌላቸው ውጤት ማስመዝገብ አልቻሉም። ከአራት ዓመት በኋላም በተመሳሳይ የሮም ኦሊምፒክ ላይ በአትሌቲክስ ሀገራቸውን ወክለዋል።

ንጉሴ ከሜልቦርን መልስ ወደቀድሞ ስራቸው ቢመለሱም ኮንፌዴሬሽኑ እንደቀድሞው ደመወዝ ሊከፍላቸው ባለመቻሉ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በስፖርት መምህርነት በመቀጠር እስከ 1953 ዓ.ም ድረስ ማገልገላቸውን በታሪካቸው ዙሪያ የተፃፉ የተለያዩ መረጃዎች ያስረዳሉ። በቀጣዩ ዓመት ደግሞ በቼኮዝላቫኪያ የትምህርት ዕድል በማግኘት የአካል ማሰልጠኛና ስፖርት ትምህርት የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ከስድስት ዓመታት በኋላም ወደሀገራቸው በመመለስ በኢትዮጵያ ስፖርት ኮንፌዴሬሽን በአትሌቲክስ ስፖርት ባለሙያ ሆነው ለዘጠኝ ዓመታት ሰርተዋል። ኮንፌዴሬሽኑ ኋላ ላይ ወደ ኮሚሽንነት ሲቀየርም የተመሰገኑበትን ሥራ አከናውነዋል።

ከስፖርት አመራርነት ባለፈ በስልጠናውም ይሳተፉ የነበሩት ንጉሴ ሮባ በ1968ቱ የሜክሲኮ ኦሊምፒክ በአስመራ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድንን ከስዊድናዊው ዋና አሰልጣኝ ኦኒ ኒስካነን ጋር በመሆን በስልጠናው ቆይተዋል። ወጣቱ አሰልጣኝ ንጉሴ ሳይንሳዊ አሰለጣጠንን ተግባራዊ በማድረጋቸውም ተሳትፎው አጠራጣሪ በነበረው 4ኛው የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ተሳትፎ በ10ሺ ሜትር የብር እና በማራቶን የወርቅ ሜዳሊያ በማስመዝገብ ተመልሷል። በአሰልጣኝነት ዘመናቸውም እንደ ሻምበል ምሩጽ ይፍጠር የመሰሉ አትሌቶችን ለስኬታማነት በማበቃትም ስማቸው ይነሳል።

ምሩፅ በሙኒክ ኦሊምፒክ 10ሺ ሜትር የነሐስ ሜዳሊያ ሲያጠልቅ፣ ኢትዮጵያም ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ጋር በመሆን በደቡብ አፍሪካዊያን ላይ የሚፈጸመውን በደል ተቃውማ ራሷን ከውድድሩ ባገለለችበት የሞንትሪል ኦሊምፒክ እንዲሁም ምሩጽ በ5ሺ እና 10 ሺ ሜትር የወርቅ ሜዳሊያዎችን ባገኘበት የሞስኮ ኦሊምፒኮችም ንጉሴ ሮባ በዋና አሰልጣኝነት ብሄራዊ ቡድኑን መርተዋል። ቀጣዮቹ የሎስአንጀለስ እና የሴኡል ኦሊምፒኮች ላይ ኢትዮጵያ ባትሳተፍም ባርሴሎና ላይ ግን በቡድን መሪነትና አሰልጣኝነት ተሳትፈዋል። በአጠቃላይ የአሰልጣኝነት ግልጋሎታቸውም ሻምበል አበበ ቢቂላን ጨምሮ በማሞ ወልዴ፣ መሐመድ ከድር፣ እሸቱ ቱራ፣ በላይነህ ዴንሳሞ እና አበበ መኮንን የመሳሰሉ አንጋፋ እንዲሁም በርካታ ምርጥ ሴት አትሌቶችን ማፍራት ችለዋል።

ማርሽ ቀያሪው ምሩጽ ይፍጠር የወርቅ ጫማ መሸለሙ እንዲሁም በላይነህ ዴንሳሞ በማራቶን የዓለም ክብረወሰንን ለመስበሩም የአንጋፋው አሰልጣኝ ንጉሴ ሮባ ሳይንሳዊ ዘዴን የተከተለ አሰለጣጠን ከፍተኛ ድርሻ አለው። ከኢትዮጵያዊያን ባለፈም ሌሎች አፍሪካዊያን አትሌቶችንም ማሰልጠን ችለዋል። በውጤታማ ስልጠናቸውም የጥቁር አባይ ኒሻን ሲሸለሙ፤ በላይነህ ዴንሳሞ ክብረወሰን እንዲሰብር ምክንያት በመሆናቸው በሮተርዳም ማራቶን አውቶሞቢል ተበርክቶላቸዋል። በተጨማሪም ከዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ፣ የዓለም አትሌቲክስ እና ሌሎች ተቋማት የምስክር ወረቀቶችና ዲፕሎማዎችንም አግኝተዋል።

በሩብ ክፍለ ዘመን የአሰልጣኝነት ቆይታቸው ከምርጥ አትሌቶች ባለፈ እንደ እነ ዶክተር ወልደመስቀል ኮስትሬ ያሉ በኦሊምፒክና በዓለም ቻምፒዮና ገናና ስም ያተረፉ አሰልጣኞችንም በማፍራትና ልምዳቸውን በማካፈል የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በስኬት ጎዳና እንዲቀጥል አድርገዋል። የአንድ ወንድና አራት ሴት ልጆች አባት የነበሩት አሰልጣን ንጉሴ ሮባ ባደረባቸው ህመም በ1985ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ኦሊምፒክ በመጣ ቁጥር ግን ስማቸው ህያው ሆኖ ይታወሳል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር
Ministry of Labor and Skills
ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየ15 ቀኑ የሚታተም

# ከተናጠል ሩጫ ወደ አንድ መሮጫ - ሰመር ካምፕ

ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እንድትቀየር አዳዲስ ፈጠራዎች እና የለሙ ቴክኖሎጂዎች ያበረከቱት አስተዋጽኦ ወደር እንደሌለው ይነገራል። ሀገራትም የኢኮኖሚ፣የጦር እና መሰል አቅሞቻቸውን የሚያፈረጥሙት ይህንኑ የፈጠራ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም እንደሆነ ይታወቃል። ለቴክኖሎጂ ልማት ትኩረት ሰጥቶ መስራት እጅግ ውስብስብ እየሆነ በሚገኘው ዓለም ውስጥ ተደማጭም ተወዳዳሪም ያደርጋል።

ኢትዮጵያ አዳዲስ ቴክኖሎጂ የሚያፈልቁ፣ ነባር ቴክኖሎጂዎችን የሚያሻሽሉ እና የሚቀዱ በርካታ የፈጠራ ክህሎት ያላቸው ዜጎች የሚገኙባት ሀገር ናት። በተለይ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በርካታ የፈጠራ ሥራዎች ይሰራሉ። ዐውደ ርዕይ ይካሄዳል። አበቃ። ከዛ የዘለለ የፈጠራ ሥራዎችን ወደ ውጤት የሚቀየርበት እና የሚደገፉበት አሰራር አልተዘረጋም። እነዚህ በተናጠል የሚሰሩ የፈጠራ ሥራዎች ወደ ጠቅላላ ምርት (mass production) ማስገባት ቢቻል የፈጠራው ባለቤትም ሀገርም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል።

ይህንን ክፍተት የተገነዘበው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴርም አዲስ ነገር ይዞ ብቅ ብሏል። በየክልሉ ተሰጥኦ ባላቸው ሰዎች የተሰሩ የፈጠራ ውጤቶች ወደ ምርት እና ወደ ውጤት የሚቀየሩበት፤ የፈጠራ ባለቤቶቹ በአንድ ያሰባሰበ የክረምት ልዩ ቆይታ ከሐምሌ 2015 ዓ.ም ጀምሮ (summer cump) እያካሄደ ይገኛል።

‹‹ሰመር ካምፕ ለቴክኖሎጂ ማሻሻልና ፈጠራ›› በሚል መሪ ቃል ተግባራዊ እየተደረገ ያለው መርሀ ግብር ከዚህ ቀደም የተሰሩ ነባር ቴክኖሎጂዎችን ማሻሻል ፤አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን መፍጠርና የሚፈጠርበትን መንገድ ማመቻቸት፤ሃሳብን ወደ ተግባር መቀየር ፤የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ችግር እንዲፈቱ ማገዝ፤ሕብረተሰቡን የሥራ ፈጣሪ በማድረግ የሥራ አጥነት ችግርን መቅረፍ ከዓላማዎቹ መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

**የሠመር ካምፕ ተሳታፊ ቴክኖሎጂስቶቹ በተናጠል በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና በየትምህርት ተቋማት የሠሯቸውን ተመሳሳይነት ያላቸው የፈጠራ ሥራዎች ሁሉ ወደ አንድ በማምጣት አንድ የተሻሻለ የፈጠራ ውጤት ወደ ምርት ሲቀየር በሚችል መልኩ ሲያመርቱ ቆይተዋል።፡ በዚህም መሰረት የአንደኛው ዙር የሠመር ካምፕ ተሳታዎች ቁጥራቸው ከ70 የሚልቁ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን አምርተው ማውጣት ችለዋል**

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት በጋራ ባዘጋጁት በዚህ ልዩ የክረምት ቆይታ መርሐ ግብር (summer cump) የአዳዲስ ሃሳብ ፈጠራ ባለቤቶችንና ኢኖቬተሮችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ የፈጠራ ውጤቶቻቸውን ለፍሬ የማብቃት ታላቅ ዓላማን አንግቦ ለአንድ ዓመት ቆይታ አድርጓል።

የሠመር ካምፕ ተሳታፊ ቴክኖሎጂስቶቹ በተናጠል በቴክኒክና ሙያ ተቋማትና በየትምህርት ተቋማት የሠሯቸውን ተመሳሳይነት ያላቸው የፈጠራ ሥራዎች ሁሉ ወደ አንድ በማምጣት አንድ የተሻሻለ የፈጠራ ውጤት ወደ ምርት ሊቀየር በሚችል መልኩ ሲያመርቱ ቆይተዋል።፡ በዚህም መሰረት የአንደኛው ዙር የሠመር ካምፕ ተሳታዎች ቁጥራቸው ከ70 የሚልቁ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን አምርተው ማውጣት ችለዋል።

የሠመር ካምፕ መርሐ ግብር እንደ ሀገር ኢትዮጵያዊ ስሪት የሆነ ምርት እንዲመረት በማስቻል ከውጪ የሚገቡትን በሀገር ውስጥ ምርት መተካትና የውጪ ምንዛሪን ማስቀረት ደግሞ መዳረሻ ግቡ ነው።

ቴክኖሎጂስቶቹ እና የፈጠራ ባለቤቶቹ በካምፕ ቆይታቸው የሚሰሩዋቸው የፈጠራ ውጤቶቻቸው ወደ ምርት ገብተው ለገበያ የሚበቁበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል። በሀገራችን ያሉ ውጤታማ ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች በጋራና በተናጠል እንዲደግፏቸውም ተደርጓል። ሥራውን በስፋትና በጥራት መሥራት የሚያስችላቸው የብድር ድጋፍና የመስሪያ ቦታ የሚያገኙበትም ሁኔታ ይመቻችላቸዋል።

በመርሐ ግብሩ ተሳታፊዎች የፈጠራ ሃሳባቸውን የሚያዳብርና የሚያጠናክር ብሎም ምርታቸውን ለገበያ ለማቅረብ የሚያስችል የሶፍት እና ሃርድ ስኪል ስልጠናዎችን ወስደዋል። የሶፍት ስኪል ስልጠናዎች ገበያን ሰብሮ መግባትና እራሱ ምርቱን ማስተዋወቅ የሚያስችል ሥልጠና ሲሆን፤ የሂሳብ አያያዝ፣ የተግባቦት ክህሎትና ሌሎች ከወሰዷቸው እዚህ ላይ በምሳሌነት ሳይጠቀሱ የሚታለፉ አይደሉም።

በሌላ በኩል ሀርድ ስኪል የሚባለው የሥልጠና ዓይነት ሰልጣኞች በየአንዳንዱ ምርትና ሥራ ውስጥ ቴክኒካል ዕውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ሀገራችን ፈጠራን የሚያፈልቅ አእምሮ፣ጥበብን የሚያንፅ ልብና ተዓምር የሚሠሩ እጆች ያሏቸው በርካታ ልጆች ቢኖሯትም ፈጠራዎቻቸው ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ብቻ በሌሎች ሀገራት የተሰሩ ቴክኖሎጂዎች ተቀባይ ሀገር ሆና ቆይታለች። ይህንን ታሪክ የመቀየር ሰፊ ተስፋ የተጣለበት ይህ ልዩ የክረምት ቆይታ (ሰመር ካምፕ) የተናጠል እሩጫዎችን ወደ አንድ መሮጫ በማምጣት አቅማቸውን በማስተባበር ፍሬያቸውን ለሀገር እና ሕዝብ ለማቋደስ ከጫፍ ደርሷል።

ይሄን ሥራና ክህሎት ሚኒስቴሩ የፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም እየተከናወነ ያለን መልካም ተግባር ማስፋት፣ ማነቆዎችን መፍታት እና ድጋፍ የሚፈልጉ ሥራዎችን ለይቶ በመደገፍ በክህሎት ልማት፣ ሥራ ዕድል ፈጠራ እና በሰላማዊ ኢንዱስትሪ ግንኙነት ላይ የተቀመጡ ግቦች እንዲሳኩ የበለጠ መደላድል መፍጠር ይጠበቃል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ